# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## *የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነትን ለማስጠበቅ የዘረጋውን የአሰራር ስርዓት ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ረቂቅ ሪፖርት*

**የካቲት 2008 ዓ.ም.**

# Table of Contents

ክፍል አንድ........................................................................................................ 5
መግቢያ............................................................................................................. 5
የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አመሠራረት ................................................. 5
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ፣ ራዕይ እና ሥልጣንና ተግባር ............................................. 6
ዓላማ (Objective) ........................................................................................... 6
ራዕይ (Vision) .................................................................................................. 6
ሥልጣንና ተግባር .............................................................................................. 6
በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሠራተኞች የሙያ ድህንነትና ጤንነት ማስፈፀሚያ መመርያ ...... 7
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር አደረጃጀትና የሰው ሀይል................................ 9
የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ኃይል ........................................................................... 9
የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ...................................................................... 10
የኦዲቱ አካባቢ(potential Audit Area) ................................................................. 10
የኦዲቱ ዓላማ .................................................................................................... 10
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ(Audit Issues)............................................................. 10
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ............................................................................................. 11
የሙያ ደህንነትና ጤንነት ቡድን የሥራ ሂደት መግለጫ (Process descriptions)...... 12
ክፍል ሁለት ........................................................................................................ 14
ግኝቶች............................................................................................................. 14
2.1 የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በመከላከል መርህ ላይ ተመስርቶ በስራ ቦታዎች የሚተገበርበት እና በስራ ላይ አደጋዎች ሲከሰቱ ተገቢውን የሆነ የመልሶ ማቋቋም ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣.................................................................................................... 14
አሰሪዎች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ስለማቋቋማቸው በተመለከተ፤ ........................................................................................ 14
ድርጅቶች ለሠራተኞቻቸው የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች ልብሶች ሌሎች ቁሳቁሶችን ማቅረባቸውን በተመለከተ፤ ......................................................... 15
የድርጅቶች የስራ ቦታና ግቢ የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን በተመለከተ፤ .................................................................................. 18

አዳዲስ ድርጅቶች ሲሰሩ እና ያሉት ነባር ድርጅቶች ሲስፋፉ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 20

በድርጅቶች የሚገኙ ማንኛውንም ነገሮች ምርመራ የሚደረግበት አሰራር መኖሩን በተመለከተ፤ ........ 22

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም በስራ አካባቢ ጥበቃ ላይ ምርጥ ተሞክሮዎችን ስለመለየቱ በተመለከተ፤ ........ 23

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት የቴክኒክ ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ማሰራጨቱን በተመለከተ፤ ........ 24

በድርጅቶች ውስጥ በሰራተኞች የሚደርሰውን ማንኛውም አደጋ እና በሽታዎች አሰሪዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማሳወቃቸው በተመለከተ፤ ........ 25

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር መመሪያ ማዘጋጀት እና ማሰራጨትን በተመለከተ፤ ........ 26

የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ስልጠና አሰጣጥ በተመለከተ.... 27

2.2 የስራ ላይ አደጋዎችን እና በሥራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቅንጅታዊ አሰራር የተዘረጋ እና በዘርፉ የሚያጋጥሙ የስራ ላይ አደጋዎች፣ የጤና ችግሮች የሚያስፈልጉ የሚሰበሰቡ የሚደራጁና የሚሰራጩበት ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋናውጤታማ መገምገም፣.... 28

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ልዩ ድጋፍ በሚሹና የኢንቨስትመንት መዳረሻ በሆኑ ክልሎች የሚያደረገው እገዛ በተመለከተ፤ ........ 28

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፤ ........ 29

ትኩረት የሚሹ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች ዙሪያ ጥናትና ምርምር ማካሄድን በተመለከተ፤ ........ 30

የሁለትዮሽ እና የሦስትዮሽ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤ ........ 31

2.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከት የወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመርያዎችና አለም አቀፍ ስምምነቶችን በስራ ላይ መዋላቸውንና ውጤታማነታቸውን ለመገምገምና ለማስተካከል የሚያስችል የክትትል፣ የቁጥጥርና የግብረ መልስ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣ ........ 33

በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ በአዋጅና በሌሎች ህጎች የወጡ ድንጋጌዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፤ ........ 33

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መለኪያ እና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ተግባራዊ ማድረጋቸውን በተመለከተ፣ ........ 35

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ አካባቢ የደረሱ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶች ያስከተሉትን ስብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች በተመለከተ፣ ........ 36

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙ.ያ ዘርፍን ያገናዘበ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት መመዘኛ መስፈርት/ ስታንዳርድ/ አዘጋጅቶ ማሰራጨቱን በተመለከተ፣ ........ 37

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከተ የመረጃ ቋት (Data base) መኖሩን በተመለከተ፣ ........ 38

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራልና በክልል የሚገኙ ድርጅቶችን ዝርዝር መረጃ መያዝ በተመለከተ፣ ........ 39

የሠራተኞች የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በተመለከተ የቅሬታ አቀራረብን በተመለከተ፣ ........ 40

በሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ግንዛቤ የሚያዳብሩ ለምሳሌ ፓስተሮች፣ ብሮሸሮች እና ሌሎችም የሚሰራጭበት አሰራር መኖሩን በተመለከተ፣ ........ 41

ክፍል ሦስት ........ 43

መደምደሚያ ........ 43

3.1 የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በመከላከል መርህ ላይ ተመስርቶ በስራ ቦታዎች የሚተገበርበት እና በስራ ላይ አደጋዎች ሲከሰቱ ተገቢውን የሆነ የመልሶ ማቋቋም ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣ ........ 43

3.2 የስራ ላይ አደጋዎችን እና በሥራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቅንጅታዊ አሰራር የተዘረጋ እና በዘርፉ የሚያጋጥሙ የስራ ላይ አደጋዎች፣ የጤና ችግሮች የሚያስፈልጉ የሚሰበሰቡ የሚደራጁና የሚሰራጩበት ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋናውጤታማ መገምገም፣.... 44

3.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከት የወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመርያዎችና አለም አቀፍ ስምምነቶችን በስራ ላይ መዋላቸውንና ውጤታማነታቸውን ለመገምገምና ለማስተካከል የሚያስችል የክትትል፣ የቁጥጥርና የግብረ መልስ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣ ........ 45

ክፍል አራት ........ 47

የማሻሻያ ሀሳብ ........ 47

4.1 በሥራ ቦታዎች የሚከሰቱ አደጋዎች እና የጤና ችግሮችን ለመከላከል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣ ........ 47

4.2 የስራ ላይ አደጋዎችን እና በሥራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቅንጅታዊ አሰራር የተዘረጋ እና በዘርፉ የሚያጋጥሙ የስራ ላይ አደጋዎች፣ የጤና ችግሮች የሚያስፈልጉ ፣ የሚሰበሰቡበት፣ የሚደራጁና የሚሰራጩበት ኢኮኖሚያዊ ፣ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣ ........ 48

*4.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከት የወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመርያዎችና አለም አቀፍ ስምምነቶችን በስራ ላይ መዋላቸውንና ውጤታማነታቸውን ለመገምገምና ለማስተካከል የሚያስችል የክትትል፣ የቁጥጥርና የግብረ መልስ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣ ........ 49*

*በናሙና የተመረጡ ክልሎችና የልማት ድርጅት ዝርዝር ........ 59*

*በናሙና የተመረጡ ክልሎች ........ 59*

*በናሙናየተመረጡየድርጅቶችስምዝርዝር ........ 59*

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

### የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አመሠራረት

1. አሁን ያለው የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በመባል የሚታወቀው መ/ቤት ህዝብ በኑሮው እድገት እንዲያገኝ በተለይም አርብቶ አደሩ ህዝብ በኑሮው እንዲሻሻል ለማድረግ፣ ከኃላቀር ባህል ወይም ልምድ እንዲላቀቅ ለማስቻል በጥር ወር 1949 አ.ም" የህዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር" በመባል በአዋጅ ተቋቋመ፡፡ከ10 አመት በኃላ ደግሞ በትዕዛዝ ቁጥር 46/1958 አ.ም" የህዝባዊ ኑሮ እድገትና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር " በሚል በአዲስ ድርጅታዊ መዋቅር ተደራጅቶ የማህበራዊ ደህንነት ፣የህዝብ ኑሮ እድገት፣የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳዮችን የሚያካትቱ ስራዎችን ያከናውን ነበር:: ከየኮቲት 1966 አብዮት በኃላ በአዋጅ ቁጥር 127/1969 "የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር " በሚል ስም በአዲስ ድርጅታዊ መዋቅር እንዲሁም ስልጣንና ኃላፊነት ተቋቁማል፡፡ቀጥሎም በ1980 አ.ም በወጣው አዋጅ ቁጥር 8/1980 የመ/ቤቱ ስልጣንና ኃላፊነት በድጋሚ ተለውጧል፡፡
2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከተመሰረተ በኋላ የመ/ቤቱ ስም እና ዋና ዋና ዓላማዎቹ ሳይለወጥ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 4/1987 እንደገና ተመስርቷል፡፡ በመቀጠልም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 እንደገና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተብሎ ተቋቁሟል፡፡
3. የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ብድን የሚያከናውናቸው ስራዎች አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች ደንበኞችና በሌሎች ሕጋዊ መሰረቶች የተቀመጠለትን መሰረታዊ የሥራ ሁኔታዎችና መብቶችን እንዲጠበቁ ቁጥጥር ያደረጋል፣ የሥራ ሁኔታ ደረጃዎች ያወጣል፣ ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል እንዲከበሩ የሚያስችሉ ቁጥጥሮቾ ያደረጋለ፣ በጥናት ላይ የተመሰረተ መረጃዎች መስጠትና ሥልጠናዎች በማካሄድ የሥራ ቦታዎች ከሙያ ጠንቆች ለአደጋ የሚያጋልጡ ሠጋቶች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የሥራ ቦታ ቅኝቶች ማድረግ ፣ የሥልጠና የምክር ድጋፍ መስጠት፣ በሥራ ቦታ የሙያ ደህንነት ጤንነት አገልግሎት በሶስትዮሽና በሁለትዮሽ መርሆ እንዲራመድ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ማድረግ፣ ተከታታይና ዘላቂ በሆነ መልኩ የሥራ ቦታዎች እንዲሻሻሉ፣ የሠራተኞች ጤንነት ደህንነት እንዲረጋገጥ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲስፋፋ ማድረግ፣ በጥናትና በሥልጠና የተደገፉ ሥራዎች በመስራት በሥራ ላይ ጉዳቶች በመከላከልና የሙያ

ጤንነትና ደህንነት ባህል እንዲጎለበት በማድረግ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ የሚያስችል ሥርዓት የመዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግን ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

4. በተጨማሪ በክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የሚከናወኑ ተግባራት በድርጅቶች መሠረታዊ የሥራ ቁጥጥር ማድረግ፣ በድርጅቶች ላይ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ሁኔታ ቁጥጥር ማድረግ፣ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴዎች ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ ማድረግ፣ በልማት ድርጅቶች የሚከሰቱ የሥራ ላይ አደጎችና የሙ.ያ በሽታን መረጃ መመዝገብ እና ምርመራ ማካሄድ፣ በየኢንዲስትሪው ጥቅም ላይ የሚውሉ ከሚካሎች በሠራተኛው ደህንነት ና ጤንነት ላይ የሚያስከትሉትን ሁኔታ ሳይንሳዊ በሆነ ዜዴ ለመመርመር የሚያስችል አንድ የላባራቶሪ ማዕከል ማቋቋም፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ፣ ራዕይ እና ሥልጣንና ተግባር

### ዓላማ (Objective)

5. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተቋቋመበት ዓላማ በሀገሪቱ ፍትሀዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰሪና ሠራተኛ አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 የሚሸፈኑ አሠሪዎችና ሠራተኞች ግንኙነታቸውን በሕግ መሰረት መስርተውና መብትና ግዴታቸውን ለይተው በጋራ የሚሰሩበትን፣ ለራሳቸውም ሆነ ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋፅኦ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው፡፡

   በማህበራዊ ዘርፍ የዜጎች ማህበራዊ ደህንነት የሚጠበቁባቸውንና የሚሻሻልባቸውን ዘዴዎች በተለይም፡- የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ ሊሆኑ ስለሚችሉበት፣ አረጋዊያን እንክብካቤ ስለሚያገኙበትና ተሳትፎአቸው ሊጎለብት ስለሚችልበት፣ የማህበራዊ ችግሮችን ስለመከላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሐድሶ አገልግሎት ስለሚያገኙበት፣ ሁኔታ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ያጠናል፣ ስራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

### ራዕይ (Vision)

6. በ2017 ዓ.ም የስራ ስምሪት የተስፋፋበት ፣ ምቹ የስራ ሁኔታ የተረጋገጠበት እና ማህበራዊ ጥበቃ የተስፋፋበት ኢትዮጲያን ማየት ፡፡

### ሥልጣንና ተግባር

7. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በማቋቋሚያ አዋጁ መሰረት የተለያዩ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡እነዚህም፡-

- የኢንዱስትሪው ሰላም እንዲጠበቅ፡-

ሀ/ ሠራተኞችና አሰሪዎች በማህበር የመደራጀትና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

ለ/ በአሰሪዎችና በሰራተኞች መካከል የሁለትዮሽ እንዲሁም የመንግስት ወገንን ጨምሮ የሦስትዮሽ አሰራሮች እንዲለመዱ ያደርጋል፤

ሐ/ የሥራ ክርክሮች በተቀላጠፈ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኙ የሚያስችሉ አሠራሮችን ይዘረጋል፤

- የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ ደረጃዎችን ያወጣል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውንም ይከታተላል፤
- ቀልጣፋና ፍትሐዊ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ለውጭ አገር ሰዎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ይወስናል፣ ፈቃድ ይሰጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይቆጣጠራል፤ የኢትዮጲያውያን የውጪ ሀገር የሥራ ስምሪት አገልግሎትን ይቆጣጠራል፤
- በሀገሪቱ ውስጥ መደበኛ በሆነና መደበኛ ባልሆነ ሥራ ላይ ስለተሰማራውና በሥራ አጥነት ስለሚገኘው የሰው ኃይልና ስለሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፤ የሥራ ገበያ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፤
- በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሰራተኛና አሰሪ ማህበራት ይመዘግባል፤
- ለፌደራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሰራተኛ ማህበራትንና የህብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፤ በነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ተግባሮችን ያከናውናል፤ በአሰሪዎችና በሰራተኞች መካከል የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን በስምምነት ለመጨረስ የማስማማት አገልግሎት ይሰጣል፣
- የዜጎች ማህበራዊ ደህንነት የሚጠበቁባቸውንና የሚሻሻሉባቸውን ዘዴዎች በተለይም፡-

  ሀ/ የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ ሊሆኑ ስለሚችሉበት፣

  ለ/ አረጋዊያን እንክብካቤ ስለሚያገኙበትና ተሳትፎአቸው ሊጎለብት ስለሚችልበት፣

  ሐ/የማህበራዊ ችግሮችን ስለመከላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተሐድሶ አገልግሎት ስለሚያገኙበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ያጠናል፣ ሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

## <u>በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሠራተኞች የሙያ ድህንነትና ጤንነት ማስፈፀሚያ መመርያ</u>

8. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሠራተኞች የሙያ ድህንነትና ጤንነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 377/1996

የማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 466/97 እና 496/98 ፣ብሄራዊ የሙ.ያ ድህንነትና ጤንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ፣የስራ ሁኔታ ቁጥጥር የትግበራ ማንዋል፣አጠቃላይ የሙ.ያ ድህንነት ጤንነትና የሥራ አከባቢዎች ጥበቃ መመሪያ፣ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ አቋቋምን ለመወሰን የወጣ መመሪያ 1998 ዓ.ም፣ ለወጣት ሠራተኞች የተከለከሉ ስራዎች ዝርዝር መመሪያ 2005 ዓ.ም እና ለሴት ሠራተኞች ከባድ ወይም ለጤና ጎጂ የሆኑ ወይም የመውለድን ሁኔታ የሚያውኩ ስራዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ 2005 ዓ.ም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጁ ሰነዶች ናቸው፡፡

9. በሚኒስቴር መ/ቤቱና የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ብድን የሚያከናውነው ተግባራት የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ደረጃዎች ያወጣል፣ ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣በጥናት ላይ የተመሰረተ መረጃዎች መስጠትና ሥልጠናዎች በማካሄድ የሥራ ቦታዎች ከሙ.ያ ጠንቆች ለአደጋ የሚያጋልጡ ሠጋቶች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የሥራ ቦታ ቅኝቶች ያደረጋል፣ የሥልጠና የምክር ድጋፍ መስጠት፣ በሥራ ቦታ የሙ.ያ ደህንነት ጤንነት አገልግሎት በሶስትዮሽና በሁለትዮሽ መርሆ እንዲራመድ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ማድረግ፣ ተከታታይና ዘላቂ በሆነ መልኩ የሥራ ቦታዎች ማሻሻል፣ የሠራተኞች ጤንነት ደህንነት እንዲረጋገጥ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲስፋፋ ማድረግ፣ በጥናትና በሥልጠና የተደገፉ ሥራዎች መስራት፡፡

10. በክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የሚከናወኑ ተግባራት መሠረታዊ የሥራ ቁጥጥር ማድረግ፣ በድርጅቶች ላይ የሙ.ያ ድህንነትና ጤንነት ሁኔታ ቁጥጥር ማድረግ፣ የሙ.ያ ድህንነትና ጤንነት ኮሚቴዎች ሙ.ያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ ማድረግ፣ በልማት ድርጅቶች የሚከሰቱ የሥራ ላይ አደጋችና የሙ.ያ በሽታን መረጃ መመዝገብ እና ምርመራ ማካሄድ፣ በየኢንዱስትሪው ጥቅም ላይ የሚውሉ ከሚካሎች በሠራተኛው ድህንነት ና ጤንንት ላይ የሚያስከትሉትን ሁኔታ ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ ለመመርመር የሚያስችል አንድ የላባራቶሪ ማዕከል ማቋቋም፡፡

የሚሉት ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር አደረጃጀትና የሰው ሀይል

11. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው በተቋሙ የበላይ አመራር አካል በሆኑ በሚኒስትር እና በሁለት የሥራ ዘርፍ ሚኒስቴር ዴታዎች ሲሆን ተጠሪነቱም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡ እንዲሁም የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአንድ ሚኒስትርና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች የሚመራ ሲሆን፤ ሦስት ዋና የሥራ ሂደትና ስምንት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች እንዲሁም አንድ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ ጽ/ቤት አሉት፡፡ እነዚህም የሥራ ሂደቶች፤ ሠላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነት ማስጠበቂያ ዳይሬክቶሬት፤ የሥራ ሥምሪት አገልግሎት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት፤ የማኅበራዊ ደኅንነት ልማት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት፤ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት፤ የዕቅድ ዝግጅትና የለውጥ ትግበራ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት፤ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፤ የሰው ሃብት ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፤ የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፤ የሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፤ የኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬትና የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ናቸው፡፡

## 12. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ኃይል

13. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በጠቅላላው የሰው ኃይል በ2005 ዓ.ምእና 2006 ዓ.ም እንዲሁም በ2007 ዓ.ም573፣ 583፣ 583 የሰው ኃይል እንዲኖረው የተፈቀደለት ሲሆን በሥራ ላይ ያለው የሰራተኛ ብዛት በ2005 ዓ.ም 328 አፈፃፀሙም 57% ፣በ2006 ዓ.ም 313 አፈፃፀሙም 54% እናበ2007 ዓ.ም 330 አፈፃፀሙም 57% ነው፡፡በሚኒስቴር መ/ቤቱ አሁን በስራ ላይ ያለ የሠው ኃይል በትምህርት ዓይነት ዝርዝር

| ተ.ቁ | ዋና ዋና የሙያና የት/ት ዓይነት | በሥራ ላይ ያለው የሰው ሀይል ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ፒ.ኤ.ች.ዲ | 1 | - | 1 |
| 2 | ማስተርስ | 13 | 2 | 15 |
| 3 | ድግሪ | 55 | 34 | 89 |
| 4 | ዲፕሎማ | 17 | 40 | 57 |
| 5 | ሰርተፍኬት | - | 6 | 6 |
| 6 | ቴክኒክና ሙያ | 3 | 7 | 10 |
| 7 | ከ9-12 | 23 | 43 | 66 |
| 8 | ከ1-8 | 28 | 31 | 59 |
| 9 | ማንበብና መፃፍ | 4 | 7 | 11 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ጠቅላላ ድምር | 144 | 170 | 314 |

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

14. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ከመንግሥት ግምጃ ቤት የሚመደብ ሲሆን በ2005፣ በ2006 እና በ2007 በጀት ዓመታት አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ዓ.ም | የበጀት ዓይነት | የፀደቀው በጀት በብር | ወጪ በብር | በመቶኛ% |
|---|---|---|---|---|
| 2005 | መደበኛ በጀት | 18,729,470.36 | 17,035,743.08 | 90.9 |
| 2006 | መደበኛ በጀት | 23,143,551.16 | 20,433,090.61 | 88.3 |
| 2007(9 ወር) | መደበኛ በጀት | 26,594,108.72 | 15,672,498.23 | 58.9 |

## የኦዲቱ አካባቢ(potential Audit Area)

15. ለኦዲቱ የተለየው የኦዲት አከባቢ የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ለማስጠበቅ የዘረጋው የአሰራር ስርዓት ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

16. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የአሰራር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተካሄደ መሆኑን በመገምገም የስራ ላይ አደጋዎችን እና በስራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን መንስኤቻቸውን በመለየት ችግሮቹን ለመፍታትና በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ(Audit Issues)

17. ከላይ በተገለፀው የኦዲት ዓላማና በተለየ የኦዲት አከባቢ መሰረት በማድረግ ሶስት ዋና ዋና እና ሶስት ንዑስ ኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፦

1. የስራ ላይ አደጋዎችን ለመከላከል እና በስራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ በሽታዎችን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

1.1 የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በመከላከል መርህ ላይ ተመስርቶ በስራ ቦታዎች የሚተገበርበት ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

1.2 የስራ ላይ አደጋዎችና በሽታዎች በአምራቹ የሰው ኃይልና በኢኮኖሚ እድገት ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከልና ለማስወገድ እንዲሁም ችግሮችንሲከሰቱ ተገቢ የሆኑ የህክምና፣ የጉዳት ካሳ እና የመልሶ ማቋቋም ስርዓት ተዘረግቶ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

2. የስራ ላይ አደጋዎችን እና በሥራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቅንጅታዊ አሰራር የተዘረጋ እና በዘርፉ የሚያጋጥሙ የስራ ላይ አደጋዎች፣ የጤና ችግሮች የሚያስፈልጉ የሚሰበሰቡ የሚደራጁና የሚሰራጩበት ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋናውጤታማ መገምገም፣

2.1 በሥራ ቦታዎች የሚከሰቱ አደጋዎች እና የጤና ችግሮች ለመከላከል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

2.2 የሠራተኞች የሙያ ጤንነትና ድህንነት የሚመለከቱ መረጃዎችን የሚሰበሰቡበት የሚደራጁበትና የሚሰራጩበት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ስርዓት ተግባራዊ መደረጉ መገምገም፣

3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከተ የወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመርያዎችና አለም አቀፍ ስምምነቶችን በስራ ላይ መዋላቸውንና ውጤታማነታቸውን ለመገምገምና ለማስተካከል የሚያስችል የክትትል፣ የቁጥጥርና የግብረ መልስ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣

## <u>የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ</u>

18. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡ የዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ 2005 እስከ 2007 በጀት ዓመት ያለውን ጊዜ ዝርዝር ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጲያ ፌዴራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር መ/ቤት ነው፡፡

19. ለኦዲቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎም ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ከአዲስ አበባ መስተዳደር ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ፣ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከክልሉ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል

ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ፣ እንዲሁም በናሙና ከተመረጡ የልማት ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት፣ የኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን፣ብሄራዊ ትምባሆ አክሲዮን ማህበር ፤ የግል ድርጅቶች ማለትምተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ፣ ባማኮ ኢንጂነሪነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ፣ክሌቨር ፍላወር ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ማህበራት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር ኮንፌደሬሽን፣ የኢትዮጵያ አሰሪዎች ፌደሬሽን፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ህንፃ ተቋራጭ ማህበር እና የኢትዮጵያ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራችና ላኪዎች ማህበር የስራ ኃላፊዎችን ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ መረጃዎችን በመከለስና የመስክ ጉብኝት በማድረግ መረጃዎች ተሰብስቧል፡፡

## <u>የሙያ ደህንነትና ጤንነት ቡድን የሥራ ሂደት መግለጫ (Process descriptions)</u>

20. በሰላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ማስጠበቂያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ውስጥ አንዱ የስራ ክፍል የሙያ ደህንነትና ጤንነት የስራ ክፍልሲሆን በቡድኑ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች ደንበኞችና በሌሎች ሕጋዊ መሰረቶች የተቀመጠለትን መሰረታዊ የሥራ ሁኔታዎችና መብቶችን እንዲከበሩ የሚያስችሉ ቁጥጥሮች ማድረግ፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ሥራ ሁኔታ ደረጃዎች ያወጣል፣ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ በጥናት ላይ የተመሰረተ መረጃዎች መስጠትና ሥልጠናዎች በማካሄድ የሥራ ቦታዎች ከሙያ ጠንቆች ለአደጋ የሚያጋልጡ ሠጋቶች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የሥራ ቦታ ቅኝቶች ያደረጋል፣ የሥልጠና የምክር ድጋፍ መስጠት፣ በሥራ ቦታ የሙያ ደህንነት ጤንነት አገልግሎት በሶስትዮሽና በሁለትዮሽ መርሆ እንዲራመድ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፣ ተከታታይና ዘላቂ በሆነ መልኩ የሥራ ቦታዎች እንዲሻሻሉ፣ የሠራተኞች ጤንነት ደህንነት እንዲረጋገጥ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲስፋፋ ማድረግ፣ በጥናትና በሥልጠና የተደገፉ ሥራዎች በመስራት በሥራ ላይ ጉዳቶች በመከላከልና የሙያ ጤንነትና ደህንነት ባህል እንዲጎለበት በማድረግ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ የሚያስችል ሥርዓት የመዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግን ትኩረት ያደረገ ነው፡፡
21. በተጨማሪ በክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የሚከናወኑ ተግባራት በድርጅቶች መሠረታዊ የሥራ ቁጥጥር ማድረግ፣ በድርጅቶች ላይ የሙያ ድህንነትና ጤንነት ሁኔታ ቁጥጥር ማድረግ፣ የሙያ ድህንነትና ጤንነት ኮሚቴዎች ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ ማድረግ፣

በልማት ድርጅቶች የሚከሰቱ የሥራ ላይ አደጎችና የሙያ በሽታን መረጃ መመዝገብ እና ምርመራ ማካሄድ፣ በየኢንዱስትሪው ጥቅም ላይ የሚውሉ ከሚካሎች በሠራተኛው ድህንነት ና ጤንንት ላይ የሚያስከትሉትን ሁኔታ ሳይንሳዊ በሆነ ዜዴ ለመመርመር የሚያስችል አንድ የላባራቶሪ ማዕከል ማቋቋም፡፡

# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## 2.1 የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በመከላከል መርህ ላይ ተመስርቶ በስራ ቦታዎች የሚተገበርበት እና በስራ ላይ አደጋዎች ሲከሰቱ ተገቢውን የሆነ የመልሶ ማቋቋም ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

### አስሪዎች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ስለማቋቋማቸው በተመለከተ፤

22. አስሪዎች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ በተቋማቸው ስለማቋቋማቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

23. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መዝግቦ ከያዛቸው 40 የልማት ድርጅቶች ውስጥ አስራ አንዱ ድርጅቶች ማለትም በግዥ አገልግሎት ድርጅት፣ የኢትዮጲያ ማዕድን አክሲዮን ማህበር፣ ተፋጥሮ ሙጫ ምርት ፣የኢትዮጲያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት፣ ባቱ ኮንስትራክሽ አክሲዮን ማህበር፣ ኮንስትራክሽን ቢዝነስ ባንክ ፣ የኢትዮጲያ መድሃኒት ፋብረካ፣ ህንፃ እቃዎች አቅራቢ ድርጅት ፣ የኢትዮጲያ ምድር ባቡር ኮርፓሬሽን፣ ፐብሊክ ትራንስፓርት ድርጅት እና የኢትዮጲያ ባህር ሎጀስቲክ አገልግሎት የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ያላቋቋሙ መሆኑ ታውቋል፡፡

24. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ድጋፍና ክትትል የሚደረግላቸው ድርጅቶች 44 መሆናቸውን እና ከነዚህ ውስጥ 33 ድርጅቶች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴዎች እስከ 2008 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ አመት ድረስ የተቋቋመባቸው መሆኑ፣ ኮሚቴው ያልተቋቋመባቸው ስድስት ድርጅቶች ማለትም በግዥ አገልግሎት ድርጅት ፣ ለኢትዮ ፕላስቲክ ድርጅት ፣ የኢትዮጲያ ምድር ባቡር ኮርፓሬሽን ፣ በባህር ትራንስፓርትና ሎጀስቲክ አገልግሎት ፣ በኢትዮጲያ ኮሚዲቲ ኤክስቼንጅ( ESEX) እና የቃሊቲ ብረታብረት ፋብረካ ብቻ መሆናቸውን፤ እንዲሁም በአንዳንድ ድርጅቶች ቀደም ሲል የመቋቋም ስራ የተከናወነባቸው መሆኑ ነገር ግን በመዋቅር ለውጥና በባለሙያዎቸ ስራ መልቀቅ ምክንያት በየጊዜው ኮሚቴዎች በመፍረስና በስራ ላይ ያለመሆን ችግር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

25. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም በአምስቱ ላይ የተቋቋመባቸው ስለመሆኑ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ የሰጡትም ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

26. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፖርት ላይ የተሰጠ ምላሽ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ያላቋቋሙ ተብለው ከተጠቀሱ ድርጅቶች በግዥ አገልግሎት ድርጅት ጥር 1/2007 ዓ.ም ፣ በህንፃ አቅራቢዎች ድርጅት በጥቅምት 28/2007 ዓ.ም፣ በባቱ ኮንስትራክሽን ስኔ 25/2005 ዓ.ም ፣ ለተፈጥሮ ሙጫ ምርት ስኔ 19/2007 ዓ.ም እና በባህር ትራንስፓርት እና ሎጂስቲክ አገልግሎት መጋቢት 2/2007 ዓ.ም በተፃፈው የቁጥጥር መመሪያ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት የድጋፍ አገልግሎት መሠረት ደብዳቤዎች ኮሚቴው እንዲያቋቁሙ መመሪያ የተሰጠ መሆኑን፡፡ ስለሆነም አምስት ድርጅቶች የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ያልተቋቋመበት ምክንያት የተገለፀው የመዋቅር ለውጥና የባለሙያዎች ስራ መልቀቅ ተጠቃሽ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

27. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፉዎች ይህንን ቢሉም ስለስድስቱ ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጲያ ማዕድን አክሲዮን ማህበር፣ የኢትዮጲያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት፣ ኮንስትራክሽን ቢዝነስ ባንክ ፣ የኢትዮጲያ መድሃኒት ፋብረካ ፣ፐብሊክ ትራንስፓርት ድርጅት እና የኢትዮጲያ ምድር ባቡር ኮርፓሬሽን የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ስለመኖራቸው የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ፡፡

28. ስለሆነም አሰሪዎች የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ባለማቋቋቸው ምክንያት ሠራተኞች ስለሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ማወቅ ያለባቸውን ግንዛቤ እንዳይኖራቸውና በስራ ላይ ለሚደርስ አደጋ የተጋለጡ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## ድርጅቶች ለሠራተኞቻቸው የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች ልብሶች ሌሎች ቁሳቁሶችን ማቅረባቸውን በተመለከተ፤

29. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅቶች ለሠራተኞቻቸው የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ልብስና ሌሎች ቁሳቁሶችን ማቅረባቸውንና ስለአጠቃቀሙ መመሪያ (ስልጠና) የሚሰጡበት አሰራር መኖሩን እና ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

30. ይሁን እንጂ በናሙና ከተመረጡ 11 ድርጅቶች ውስጥ 8ቱ ማለትም የኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት፣ የኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፓሬሽን፣ ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ባማኮ ኢንጂነሪነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ልብስና ሌሎች ቁሳቀሶችን የማያቀርቡ መሆናቸው እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱና በክልል

ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ክትትልና ድጋፍ የማይደረግ መሆኑ ጉዳዩ አስመልክቶ በኦዲት ቡዱኑ ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

31. የኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት ለሠራተኞች የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ልብስና ሌሎች ቁሳቁሶችን የማያቀርብ በመሆኑ ሠራተኞች ለከፍተኛ የአካል ጉዳት ብሎም ለሞት እየተዳረጉ መሆናቸውን በአካል በባልቻ ሆስፒታል በመገኘት ለመረዳት ተችሏል፡፡

32. የኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት ድርጅት በ2007 ዓ.ም በሠራተኞች ላይ በደረሰ የአካል ጉዳት ለህክምና እና ለሞት ብር1,034,387.83 ( አንድ ሚሊዮን ሰላሳ አራት ሺ ሶስት መቶ ሰማንያ ስባት ከሰማንያ ሶስት ሳንቲም) የካሳ ክፍያ የከፈለ መሆኑ፣ በስራ ላይ በደረሰ አደጋ ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሠራተኛ ለአካል ጉዳት የተጋለጠ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡የ2005 እና የ2006 ዓ.ም ማስረጃዎች እንዲቀርቡ በኦዲቱ ወቅት በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም መረጃውን ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡

33. የእህል ንግድ ድርጅት እህሉ ነቀዝ እንዳይበላው ኬሚካል በመርጨት ላይ የነበሩ ሠራተኞች ያለ ምንም መከላከያ ስራቸውን ሲያከናውኑ በመስክ ምልከታ ወቅት ታይቷል፡፡



ምስል 1፡- በኢትዮጲያ እህል ንግድ ድርጅት ለእህሉ የነቀዝ መከላከያ ኬሚካል ተረጭቶ ያለ ምንም የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ስራቸውን ሲያከናውኑ



ምስል 2፡- በኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ማለትም የአቧራ መከላከያ፣ ጋውን፣ ጓንት እና የመሳሰሉትን ሳይጠቀሙ ስራቸውን ሲያከናውኑ

34.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በድርጅቶች የሚካሄድ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን ሠራተኞች በተሟላ ደረጃ ማግኘታቸውንና መጠቀማቸውን አስመልክቶ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን፣ ሆኖም ግን በበርካታ ተቋሞች የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች አሰጣጥና አጠቃቀም ላይ ክፍተት ያለበት መሆኑን በክትትልና ቁጥጥር ወቅት የተመለከቱ መሆኑን፤ ችግሩንም ለመቅረፍ መመሪያና ማስጠንቀቂያ በመስጠት እንዲሻሻሉ ጥረት የተደረገ መሆኑን፣ይሁን እንጂ በአንዳንድ ተቋሞች አሠሪዎች የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን ለሠራተኞች በተለይም ለኮንትራትና ለጊዜያዊ ሠራተኞ ያለመስጠት ችግር መኖሩን ገልፀዋል፡፡

35.የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም በመስክ ምልከታ ወቅት ከታዩ ድርጅቶችውስጥ ቦማኮ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር፣ ተክለብርሃን አንባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር፣የኢትዮጵያ ውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን፤-የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት፡ የኢትዮጲያ ኤሌትሪክ አገልግሎት ሠራተኞች ቋሚም ሆኑ ኮንትራት ሠራተኞች የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ልብስና ሌሎች ቁሳቁሶች ያልቀረበላቸው መሆኑ በኦዲት ወቅት የታወቀ በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

36.ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና አልባሳት አሰጣጥና አጠቃቀምን በተመለከተ በማሳያነት ድርጅቶች ተዘረዝረው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ እንደማያደረግ በሪፓርቱ ተጠቅሷል ከዚህም አኳያ ለኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ጥር 30 ቀን 2006 ዓ.ም ፣ለኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት ታህሳስ 18 ቀን 2006 ዓ.ም ፣ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት መስከረም 22

ቀን 2006 ዓ.ም ፣ በኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ.ም ለድርጅቶች የአደጋ መከላከያ መሳሪያ እንዲያሟሉ ትዕዛዝ የተላለፈ መሆኑ ፡፡በመሆኑም በኢትዮጲያ መብራት አገልግሎትና በኢትዮጲያ እህል ንግድ ድርጅት የታየው በበርካታ ተቋሞች የሚታይ ሲሆን ችግሩን እንዲቃለል የምናደረገው ተከታታይ ጥረት ግን የማቋረጥ መሆኑ የገለፁ መሆኑ፡፡

37. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም የኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት እና የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ሚኒስቴር መ/ቤት ድርጅቶቹ የአደጋ መከላከያ አልባሳትና ቁሳቁሶችን እንዲያሟሉ ትዕዛዝ ቢያስተላልፍም የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ ባደረገበት ወቅት ድርጅቶች ለሠራተኞች ምንም የአደጋ መከላከያ አልባሳትና የአደጋ መከላከያ ቁሳቁስ ያልቀረበላቸው መሆኑ በኦዲት ወቅት የታወቀ በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

38. ስለሆነም አሰሪዎች ለሠራተኞቻቸው የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ልብስና ሌሎች ቁሳቁሶችን ባለማቅረባቸው ሠራተኞች ለከፍተኛ አካል ጉዳት እና ለሞት እንዲጋለጡ እንዲሁም ድርጅቶች ለከፍተኛ የካሳ ክፍያ ወጪ እንዲዳረጉ አድርጓል፡፡

## የድርጅቶች የስራ ቦታና ግቢ የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን በተመለከተ፤

39. የድርጅቶች የስራ ቦታና አካባቢ የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ለማስጠበቅ የሚያግዙ የማስተማሪያና የማስጠንቀቂያ ማስታወቂያዎች ስለመለጠፋቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ቦታዎችና አካባቢዎችን ደህንነትን መጠበቃቸውን አስመልክቶ ቁጥጥር ሊያካሂድባቸው ከሚገባው ድርጅቶች መካከል በናሙና ከተመረጡ 11 ድርጅቶች ውስጥ 4ቱ ማለትም የኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት እና የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የስራ ቦታና ግቢ የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ስራዎች በሚከናወኑባቸው ቦታዎች ላይ ሊለጠፉ የሚገባቸው ማስታወቂያዎች የማስተማሪያና የማስጠንቀቂያ ያልተለጠፉ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ መስክ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

41. ከዚህም በተጨማሪ እህል ንግድ ድርጅት ሳሪስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተለያዩ መጋዝኖች ያሉና በውስጣቸው ብዛት ያላቸው ጊዜያዊ ሠራተኞች የሚሠሩት ቢሆንም በዚህ የስራ አካባቢ የሠራተኞች ጤንነትን ለማስጠበቅ የሚያስችል ደረጃውን የተጠበቀ የመፀዳጃ ቤት ባለመኖሩ ምክንያት ሠራተኞች በግቢ ውስጥ የሚፀዳዱበት ሁኔታዎች መኖራቸው፣ እንዲሁም በግቢ

ውስጥ ለረዥም ጊዜ የተከማቸ ቆሻሻ በመኖሩ የሠራተኞች ጤንነት ለአደጋ በተጋለጠ ሁኔታ እንደሚገኝ የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው በመስክ ምልከታ ግምገማ ለማወቅ ተችሏል፡፡



ምስል 3፡- በኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት በግቢ ውስጥ ያለውን ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ

42.በሌላ በኩል በውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ተሽከረካራዎች የጥገና ጋራዥ ሠራተኞች የመኪና ቀለም የሚቀቡበት ስፍራ ራሱን የቻለ ባለመሆኑ ቀለም በሚቀባበት ወቅት በሌላ ዘርፍ ያሉ ሰራተኞች ከቀለሙ በሚወጣ ሽታና ብናኝ ጤንነታቸውን ለአደጋ  የተጋለጠ በመሆናቸው የኦዲት ቡድኑ በድርጅቱ ተገኝቶ ባካሄደው ግምገማ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

43.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በድርጅቶች የስራ ቦታና ግቢ ሊለጠፍ የሚገባቸው የሠራተኞች የደህንነትና ጤንነት የተመለከቱ ማስታወቂያዎችን( ፓስተሮችን፣ ብሮሸሮችን እና በራሪ ምልክቶችን ) በተለያዩ የሴፉቲ ጉዳዮች ዙሪያ እየተዘጋጁ እየታተሙና ለድርጅቶች እየተሰራጨ የሚገኙ መሆኑ ነገር ግን በህትመት ውስንነት ምክንያት ለሁሉም ድርጅቶች የሴፊቲ ፓስተሮችን የማሠራጨት ሁኔታ ክፍተት ያለባቸው መሆኑ ገልፀዋል፡፡

44.የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም በኦዲቱ በታዩ ድርጅቶች ያልተሟሉ ከመሆናቸው በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ  ከፓስተሮች፣ ብሮሸሮች እና በራሪ ምልክቶች

ድርጅቶች በስራ መስሪያ ቦታዎች አስፈላጊ ማስታወቂያዎች መለጠፋቸውን ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም ድጋፍ ሊያደርግ የሚገባ በመሆኑ የተሰጠው መልስ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

45. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ በድርጅቶች የስራ ቦታና ግቢ ሊለጠፍ የሚገባቸው የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ፓስተሮች፣ ብሮሸሮችና በራሪ መልዕክቶች በዋናነት በአስሪው እየተዘጋጁ መለጠፍ ያለባቸው ቢሆኑም ተግባራዊነቱን ተከታትሎ በማረጋገጥ በኩል የአቅም ውስንነት ስላለ አንዳንድ ክፍተቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

46. ስለሆነም የድርጅቶች የስራ ቦታና ግቢ የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን የሚረጋገጥበት የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት አለመጠናከረና የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነትን ለመጠበቅ የሚያዙ የማስጠንቀቂያና የማስተማሪያ ማስታወቂያዎች በተገቢው ቦታዎች  ሊለጠፍ የሚገባቸው ማስታወቂያዎች ባለመለጠፋቸው ሠራተኞች ስለ ስራ ቦታቸው በቂ መረጃ እንዳይኖራቸው በማድረግ ለተለያዩ አደጋዎች እና በሽታዎች እንዲጋለጡ አድርጓል፡፡

## አዳዲስ ድርጅቶች ሲሰሩ እና ያሉት ነባር ድርጅቶች ሲስፋፉ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆኑን በተመለከተ፤

47. አዳዲስ ድርጅቶች ሲሰሩ ያሉት ነባር ድርጅቶች ሲስፋፉና ሲለወጡ ወይም መሳሪያዎች ሲተከሉ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

48. ይሁን እንጂ በናሙና በተመረጡ 11 ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጲያ ኤሌትሪክ አገልግሎት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፓሬሽን ፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ የኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት እና ብሄራዊ ትምባሆ አክሲዮን ማህበር ፣ ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን፣ ባማኮ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተየግል ማህበር፣ ዛምራ ኮንስትራክሽን  አክሲዮን ማህበር ፣ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር፣ ክሌቨር ፍላወር ኃ/የተ/የግል ማህበር ድርጅቶች ሲስፋፉና አዳዲስ መሳሪያዎች ሲተከሉ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎችበየወቅቱ ክትትልና ቁጥጥር ያልተደረገ መሆኑን በኦዲቱ ታውቋል፡፡

49. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስበአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ 377/96 አንቀፅ 177/7 መሠረት አዲስ ድርጅቶች ሲሰሩ የነበሩት ሲስፋፉ ፣ ሲለወጡ ወይም መሳሪያዎች ሲተከሉ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር ከማድረግ አኳያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ

ከኢትዮጲያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ጋር ባደረገው ስምምነት ኢንቨስትመንትን ከማቀላጠፍ አኳያ ለባለሀብቶች የአንድ መስኮት አገልግሎት የመስጠት አቅጣጫ በመከተል የድርጅቶችን መቋቋም ወይም መስፋፋት ሲኖር መታየት ያለባቸውን የሠራተኛ ደህንነትና ጤንነት ቅድመ ሁኔታዎችን ( የአስቸኳይ ጊዜ መውጫ በሮች፣ የመታጠቢያና የመፀዳጃ ዝግጅቶች ) በንድፍና በፕላን ደረጃ መኖራቸውን የማረጋገጥ ሁኔታ እንደመስፍርት ተፈፃሚ ሊደረግ የሚገባ መሆኑን ለኤጀንሲው በማስታወቅ ባለሀብቶች ፍቃድ በማውጣት ሂደት እነዚህን ነጥቦች ከግንዛቤ እንዲያስገቡና ተግባራያዊ እንዲያደረጉ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ፕሮጀክቶች ወደ ተግባር ሲሸጋገሩ ለሚኒስትር መ/ቤቱ በደብዳቤ በማሳወቅ መስፈርቶቹ መከበራቸውን እንዲረጋገጥ የሚያሳውቅ ሲሆን በዚህ ላይ ተመስርቶ ለፌዴራልና ለከተማ አስተዳደር የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ አስፈፃሚ አካላት ጉዳዩን ተረድተው ቁጥጥር እንዲያካሂዱ የሚደረግ የአሰራር ስርዓት መኖሩን ገልፀዋል፡፡

50. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ጋር ያደረገው ስምምነት ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ በመሆኑ እና በኦዲት ወቅት በታዩት አስራ አንድ ድርጅቶች በስራ ኃላፊው እንደተገለፀው ተደረገ የተባለው ቁጥጥር የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ የሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡
51. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ አዳዲስ ድርጅቶች ሲሰሩ ፣ ነባር ድርጅቶች ሲስፋፉና ሲለወጡ ወይም መሳሪያዎች ሲተከሉ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ ጉዳት የማያደርሱ ስለመሆናቸው በመ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ የቀረበው ጥያቄ በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢትዮጲያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ጋር እያከናወነ ከሚገኘው ቅንጅታዊ አሰራር ጋር በተያያዘ በወቅቱ የተደረገውን ስምምነት ለማቅረብ ያልተቻለ ቢሆንም በዚህ ዙሪያ ሁለቱ መ/ቤቶች በጋራ እየተሰሩ ያሉ ሰራዎች ማስረጃ ማቅረብ ባንችልም ስራዎቹ መከናወናቸው በማሳያነት ሊወሰዱ የሚገባ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
52. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ጋር በጋራ ስራዎቹ መከናወናቸው ማስረጃ ባለማቅረባችሁ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡
53. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ አዳዲስ ድርጅቶች ሲሰሩ ያሉት ነባር ድርጅቶች ሲስፋፉና ሲለወጡ ወይም መሳሪያዎች ሲተከሉ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ጉዳት እንዳያደርሱ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች በኩል ክትትልና ድጋፍ የማያደርጉ በመሆኑ ሰራተኞች የተለያዩ የስራ ቦታ ለተለያዩ አደጋዎች እንዲጋለጡ ያደረጋል፡፡

## በድርጅቶች የሚገኙ ማንኛውንም ነገሮች ምርመራ የሚደረግበት አሰራር መኖሩን በተመለከተ፤

54. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት ድርጅቶች የሚገኙ ማንኛውንም ነገሮች ማለትም ጥሬ እቃዎች፣ የሚመረቱ ምርቶች በመጠኑ (sampling) ተወስደው በሠራተኞች ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆኑን ከሚመለከተው አካል ጋር ምርመራ ሊያደረጉ ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት ድርጅቶች የሚገኙ ማንኛውንም ነገር ማለትም ጥሬ እቃዎች፣ የሚመረቱ ምርቶች በመጠኑ (sampling) ወስደው በሠራተኞች ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆኑን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የተሰሩ ስራዎች ስለመኖራቸው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠቃሚው ከላይ የተገለፀውን ሁኔታ የሚያሳይ ማስረጃ አልተገኘም፡፡

56. ከዚህ ጋር በተያያዙ በናሙና በተመረጡ 11 ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጲያ ኤሌትሪክ አገልግሎት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፓሬሽን፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ የኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት እና ብሄራዊ ትምባሆ አክሲዮን ማህበር፣ ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን፣ ባማኮ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተየግል ማህበር፣ ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር ፣ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር፣ ክሊቨር ፍላወር ኃ/የተ/የግል ማህበር ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት ድርጅቶች የሚገኙ ማንኛውንም ነገር ማለትም ጥሬ እቃዎች፣ የሚመረቱ ምርቶች በመጠኑ (sampling) ተወስደው በሠራተኞች ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆኑን ማለትም ጥሬ እቃዎች፣ የሚመረቱ ምርቶች ምርመራ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከቀረቡ ቃለመጠይቆች እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት ድርጅት ለጤና ጎጂ የሆኑ ማንኛውም ጥሬ እቃ ምርት ወይም ቁሳቁስ በናሙና ወስዶ በሠራተኞች ላይ ጉዳት ማድረስ አለማድረሱን ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት ተግባራዊ የሚደረግበት አሰራር መኖሩን ገልፆዋል፡፡በዚህም መሰረት እንደማሳያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በተቋቋመ አንድ የጫማ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ለሶል መሳሪያ በግብአትነት ያገለግል የነበረውን የፕላስቲክ ውህድ ጥሬ እቃ በጢስ መልክ ከአየር ጋር በመደባለቅ በሠራተኞች የመተንፈሻ አካላት ላይ ጉዳት የማድረስ ውጤት በማስከተሉ ጉዳዩ በአዲስ አበባ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አማካኝነት ከስራ ቦታ በናሙና ተወስዶ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኬሚስትሪ ትምህርት ክፍል በተካሄደ የላብራቶሪይ ምርመራ ጥሬ እቃውን የመተንፋሻ አካልን አዋኪ መሆኑን የተረጋገጠ መሆኑንና ይህም የትንተና ውጤት በፓስተር ኢንስቲዩት በተደረገው የስነመርዝ ምርመራ ውህዱ ለጤና

እጅግ ጎጂ መሆኑ ስለታወቀ ጥሬ እቃው ወደ ሀገር እንዳይገባ የተደረገበት እና እርምጃ የተወሰደበት ሁኔታ መኖሩን ገልፀዋል፡፡

58. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአዲስ አበባ የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጋር በጋራ መስራታቸውን እና ተሳትፎ ማድረጋቸውን ባቀረቡት ማስረጃ ላይ የማያሳይ መሆኑ እና ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት በህጉ በተቀመጠው መሰረት አስቀድሞ የሰራተኞችን የሙያ ደህንነትና ጤንነት የማይጎዱ መሆኑ መረጋገጥ የሚገባው በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

59. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፖርት ላይ የተሰጠ ምላሽ ከስራ ቦታዎች ለጤና ጉዳት ያስከትላሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ጥሬ እቃዎችን ናሙና በመውሰድ በሠራተኞች ላይ ጉዳት የማያስከተሉ መሆኑን ምርመራ የማድረግ አሰራር ያለ ቢሆንም ፍተሻው የሚከናወነው ጥሬ እቃውን በሠራተኞች ላይ ጉዳት እንደማያደርስ ሲጠረጠር ወይም በተጨባጭ ሲታመን ይሄኑን አስመልክቶ በሚቀርበው ቅሬታ መነሻነት በመሆኑ በናሙና ከተወሰዱ ድርጅቶች ውስጥ ይህ ክስተት ባለመታየቱ የናሙና ፍተሻውን ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ያልተገኘ መሆኑ፡፡ሆኖም በአዲስ አበባ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አማካኝነት ግንቦት 2005 ዓ.ም ምርመራ የተካሄደ ሲሆን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር ስለመሰራቱ ማስረጃ አልቀረበም ለተባለው የፁሁፍ ማስረጃ ማቅረብ ባይቻልም ለቢሮው ምክርና ድጋፍ የተሰጠ መሆኑን በድጋሚ የገለፁ መሆኑ፡፡

60. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኦዲት ቡድኑ የስራ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም ሚኒስቴር መ/ቤት ከአዲስ አበባ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የተደረገውን ምርመራ በጋራ ስለማከናወናቸው የቀረበ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

61. በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማንኛውንም የሚመረቱ ምርቶችን ለምርት የሚጠቀሙበትን ግብዓት በናሙና በመውሰድ በሠራተኞች ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው በየወቅቱ ምርመራ የማይደረግባቸው በመሆኑ ሠራተኞች ለተለያዩ በሽታዎችና አደጋዎች እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም በስራ አካባቢ ጥበቃ ላይ ምርጥ ተሞክሮዎችን ስለመለየቱ በተመለከተ፤

62. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም በስራ አካባቢ ጥበቃ ላይ ምርጥ ተመክሮዎችን ሊቀምር፣ ሊያስፋፋ እና እውቅና ሊሰጥ ይገባል፡፡

63. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም በስራ አካባቢ ጥበቃ ላይ ምርጥ ተመክሮዎችን የመለየት፣ የመቀመር እንዲሁም የማስፋፋት ስራዎችን ያላከናወነ መሆኑ፣

64. ምርጥ ተመክሮ ካላቸው የሀገር ውስጥ ወይም የውጭ ድርጅቶች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት አሰራር ያልተዘረጋ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

65. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በአጠቃላይ በዘርፉ ምርጥ ተሞክሮዎችን የመለየት፣ የማስፋፋት እንዲሁም እውቅና የመስጠት አሰራር በማንዋል ተደግፎ በሴክተርና በክልል እንዲሁም በድርጅት ደረጃ ተፈፃሚ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

66. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ ምርጥ ተመክሮዎችን የመለየት ፣ የማስፋፋት እንዲሁም እውቅና የመስጠት አሰራር በአቅም ውስንነት ምክንያት ተግባራዊ እየተደረገ ባይሆንም ለወደፊቱ በተሻለ መረጃና ተጨባጭ መስፈርቶችን ላይ በመመስረት ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

67. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁምበስራ አካባቢ ጥበቃ ላይ ምርጥ ተመክሮዎች ተለይተው ያልተቀመሩና ያልተሰራጩ በመሆኑ በተሻለ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ላይ የተሰሩ ውጤታማ ስራዎች እንዳይስፋፉ ያደርጋል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት የቴክኒክ ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ማሰራጨቱን በተመለከተ፤

68. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት የቴክኒክ ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ለክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

69. ይሁን እንጂ በናሙና ከተመረጡ ሶስት ክልሎች ውስጥ ሁለቱ ማለትም የኦሮሚያ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና የደቡብ ክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት የቴክኒክ ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ያልደረሳቸው መሆኑን በኦዲት ወቅት ታውቋል ፡፡

70. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አስመልክቶ የቴክኒክ ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል በስልጠና ወቅት ለክልሎችና ለፌደራል አስፈፃሚ አካላት ያሰራጩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡የስራ ሀላፊው ይህን ቢሉም ማንዋሉን ለሁሉም ክልሎች ያሰራጩ ስለመሆኑ የሚያሳይ የፁሁፍ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

71. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት የቴክኒክ ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ሰኔ /2006 ዓ.ም በ1000 ኮፒ ታትሞ በክልልና በከተማ አስተዳደር ለሚገኙ የስራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች የተሰራጨና ስለ ማንዋሉም ቴክኒካል ይዘት ለክልሎችና ለፌደራል አስፈፃሚ አካላት በስልጠና ተደግፎ የተሰጠ መሆኑን የተገለፀ ቢሆንም ለኦዲት ቡድኑ ማንዋሉ ለሁሉም ክልሎች የተሰራጨ ስለመሆኑ የፁሁፍ ማስረጃ ባለመቅረቡ ተቀባይነት እንዳላገኘ ያመለክታል፡፡ ከዚህም አኳያ በቀጣይ የህትመት

ውጤቶችንና ትምህርታዊ ማቴሪያሎችን ለክልሎች የማሰራጨት ስራ በደብዳቤ አማካኝነት እንደሚካሄድ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

72. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የቴክኒክ ድጋፍ አስጣጥ ማንዋል ባለማሰራጨቱ ምክንያት የቁጥጥር ባለሙያዎች ወጥ የሆነ የቁጥጥር የአሰራር ስርዓት እንዳይከተሉ ያደርጋል፡፡

## በድርጅቶች ውስጥ በሰራተኞች የሚደርሰውን ማንኛውም አደጋ እና በሽታዎች አሰሪዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማሳወቃቸው በተመለከተ፤

73. በድርጅቶች ውስጥ የሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት የሚጎዱ ሁኔታዎች ሲከሰቱ እና የሚደርሰውን ማንኛውም አደጋ አሰሪዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያሳውቁበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና የሚኒስቴር መ/ቤቱም በስራ ምክንያት የሚመጡ ጉዳቶችን (በሽዎች እና አደጋዎች) የሚመዘግብበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

74. በኦዲት ወቅት በናሙና ከተወሰዱ አስራ አንድ ድርጅቶች ውስጥ ዘጠኙ (የኢትዮጲያ ኤሌትሪክ አገልግሎት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ የኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን፣ ባማኮ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተየግል ማህበር፣ ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር ፣ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር፣ ክሊቨር ፍላወር ኃ/የተ/የግል ማህበር) በሠራተኞች ላይ የሚደረሰውን አደጋ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ለክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ሪፓርት የማያደረጉ መሆኑን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

75. በናሙና የታዩት ሁሉም ድርጅቶች በስራ ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎችን ዝርዝር የሚመዘግቡበት አሰራር ስርዓት የሌላቸው መሆኑ በኦዲት ወቅት ከቀረቡ ቃለመጠይቆችና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

76. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ድጋፍና ክትትል የሚያደረግላቸው ድርጅቶች በሙሉ ሪፓርት የሚያደርጉ መሆኑን፣ ሆኖም ግን አንዳንድ አሰሪዎች በስራ ላይ የደረሰውን አደጋ ለማሳወቅ ፍላጎት የሌላቸው በመሆኑ ትክክለኛ በስራ ላይ የደረሰውን አደጋ መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን እንዲሁም በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን የሚመዘገብበት የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎች አዝጋሚ ሂደት የሚከተሉና ችግሮች ሙሉ በሙሉ ከስራ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር እንደ ሀገር ያልተዘረጋ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

77.ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፖርት ላይ የተሰጠ ምላሽ በ2005 በጀት አመት ከ233 ድርጅቶች እንዲሁም በ2006 በጀት አመት ከ236 ድርጅቶች የተሰባሰበውና የተጠናቀረው አመታዊ የስራ ላይ አደጋ ሪፖርት ማስረጃ ያቀረቡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

78.የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም የቀረበው ማስረጃ በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ የደረሰውን አደጋ በትክክል የሚገልፅ ማስረጃ ባለመሆኑ የተሰጠውን አስተያት ለመቀበል ያዳግታል፡፡

79.በመሆኑም አሰሪዎች የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት የሚጎዱ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት የሚያደርጉ አሰራር የተጠናከረ ባለመሆኑ በሀገር ደረጃ ምን ያህል ምርታማ ሠራተኛ ለአካል ጉዳትና ብሎም ለሞት እንደተጋለጠ በትክልል ማወቅ የማይቻል መሆኑን እና የችግሩን መንስኤ በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫዎች እንዳይዘረጉ አድርጎል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር መመሪያ ማዘጋጀት እና ማሰራጨትን በተመለከተ፤

80.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር መመሪያ የያዘ ሠንጠረዥ ሊያዘጋጅ፣ ሊያሰራጭ እንዲሁም በየአምስት ዓመቱ ሊያሻሽል ይገባል፡፡

81.ይሁን እንጂ በናሙና ከተወሰዱ አስራ አንድ ድርጅቶች (የኢትዮጲያ ኤሌትሪክ አገልግሎት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፓሬሽን ፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ የኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት እና ብሄራዊ ትምባሆ አክሲዮን ማህበር ፣ ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን፣ ባማኮ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ የግል ማህበር፣ ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ የግል ማህበር፣ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር እና ክሌቨር ፍላወር ኃ/የተ/የግል ማህበር) ለሁሉም በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር መመሪያ የያዘ ሠንጠረዥ ያልተሰራጨ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር መመሪያ የያዘ ሠንጠረዥ በ1999ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም በአዋጁ እንደተደነገገው በየአምስት ዓመቱ መሻሻል እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም እስካሁን ያልተሻሻለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

82.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር የያዘ መመሪያ በ1999 ዓ.ም ቢወጣም መመሪያው በበቂ ሁኔታ ለሚመለከታቸው አካላት ያልተሰራጨ እና በየአምስት ዓመቱ ያልተሻሻለ መሆኑ አስረድቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የመመሪያው ይዘት ውስብስብ በመሆኑና እና መመሪያውን ከማስፈፀም አኳያ መውጣት የሚገባቸው ጋይድላየኖችና

ፕሮሲጀሮች ያልወጡ እንዲሁም የሰለጠነ ባለሙያና ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ውስን መሆኑን ገልፀዋል፡፡

83.በመሆኑም በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር የያዘ መመሪያ በ1999 ዓ.ም ቢወጣም መመሪያው በበቂ ሁኔታ ለሚመለከታቸው አካላት ያልተሰራጨ እና በየአምስት ዓመቱ ያልተሻሻለ መሆኑ ሠራተኞች በሚሰሩት ስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ቀድመው አውቀው ጥንቃቄ እንዳይወስዱ እና ለተለያዩ በስራ ምክንያት ለሚከሰቱ በሽታዎች እንዲጠቁ ያደርጋል፡፡

## የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ስልጠና አሰጣጥ በተመለከተ

84.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች የሚሰሩት ስራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋ እንዲሁም በጤና ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ የሚያስፈልጉ ጥንቃቄዎች እና እርምጃዎች በተመለከተ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት በተግባር  የተደገፈ ስልጠና የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

85.ይሁን እንጂ በናሙና ከተመረጡ ድርጅቶች ውስጥ በዘጠኙ ማለትም የኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት፣ የኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን፣ ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ባማኮ ኢንጂነሪነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር ፣ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር እና ክላሽር ፍላወር ኃ/የተ/የግል ማህበር በቃለ መጠይቅ የሰጡት መልስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የስራ ዘርፎች ክፍተቶችን በመለየት ሠራተኞች የሚሰሩት ስራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋ እንዲሁም በጤና ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ የሚያስፈልጉ ጥንቃቄዎች እና እርምጃዎች በተመለከተ በተግባር የተደገፈ ስልጠና የሚሰጥበት አሰራር ስርዓት ባለመኖሩ ምክንያት በስራ ላይ በሠራተኞች የሚደርሰው አደጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ የጨመረ መሆኑ፤

86.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የድርጅቶቹ ክፍተቶች የሚለዩት ከስራ ቦታ ቁጥጥር እና ከቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት ከሚሰበሰቡ መረጃዎች ላይ በመመስረት እንደሆነ እና ከተቋሞች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻነት ስልጠናዎች እየተሰጡ መሆኑን፤ ሆኖም ግን እየተሰጡ ያሉ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ስልጠናዎች የአሰራር ስርዓት ከመከተል፣ በፓኬጅና በመረጃ ከመደገፍ አንፃር  ክፍተት ያለበት መሆኑን፤ ይህንን ችግር ለመቅረፍ መ/ቤቱ በስልጠና አፈፃፀም ዙሪያ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል የአሰራር መመሪያ በረቂቅ ደረጃ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡የስራ ኃላፊው ይህን ቢሉም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡ ስልጠናዎች በአዋጅ፣ፖሊሲ እና መመሪያዎች ዙሪያ

ብቻ የተሰጡ መሆናቸው ከተከለሱ የስልጠና ሪፖርት እና ቃለመጠይቅ ከቀረበላቸው ድርጅቶች ለምሳሌ ብሄራዊ ትንባሆ አክስዮን ማህበር ፣ብሄራዊ አልኮል አረቄ ፋብሪካ እና ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ለማወቅ ተችሏል፤ በመሆኑም ሠራተኞች የሚሰሩት ስራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋ እንዲሁም በጤና ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ የሚያስፈልጉ ጥንቃቄዎች እና እርምጃዎች በተመለከተ በተግባር  የተደገፈ ስልጠናዎች ያልተሰጡ በመሆኑ የሰጡትን ምልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

87. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ስልጠና አሰጣጥ መነሻ ሲያደረግ የነበረው በዋናነት ከተቋሞቹ የሚቀርቡ ጥያቄዎችና ከቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ቢሆንም ለወደፊቱ የድርጅቶችን ተጨባጭ ችግሮች እና የሴፊቲ ክፍተት ሊሸፍን በሚችል መልኩ ለመስጠት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

88. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ዘርፎችን በመከፋፈል ሠራተኞች የሚሰሩት ስራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋ እንዲሁም በጤና ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ የሚያስፈልጉ ጥንቃቄዎች እና እርምጃዎች በተመለከተ በተግባር  የተደገፈ ስልጠናዎች በየወቅቱ የማይሰጡ በመሆናቸው በስራ ላይ በሠራተኞች የሚደርሰው አደጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡

## 2.2 <u>የስራ ላይ አደጋዎችን እና በሥራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቅንጅታዊ አሰራር የተዘረጋ እና በዘርፉ የሚያጋጥሙ የስራ ላይ አደጋዎች፣ የጤና ችግሮች የሚያስፈልጉ የሚሰበሰቡ የሚደራጁና የሚሰራጨበት ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋናውጤታማ መገምገም፣</u>

### ሚኒስቴር መ/ቤቱ ልዩ ድጋፍ በሚሹና የኢንቨስትመንት መዳረሻ በሆኑ ክልሎች የሚያደረገው እገዛ በተመለከተ፤

89. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ልዩ ድጋፍ በሚሹና የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለሆኑ ክልሎች በሠራተኛ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ሊሰጥ የሚገባውን የድጋፍ ዓይነት በመለየት ሊገመግም ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ልዩ ድጋፍ በሚሹና የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለሆኑ ክልሎች በሠራተኛ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ሊሰጥ የሚገባውን የድጋፍ ዓይነት በመለየት የግምገማ ሂደት የተከናወነ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲት ወቅት ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

91.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የኢንቨስትመንት መዳረሻ በሆኑ ክልሎች የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን አስመልክቶ ትኩረት በመስጠት ክትትል የሚደረግበት አሰራር ያልተጠናከረ መሆኑን ገልፀዋል፡

92.ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ የኢንቨስትመንት መዳረሻ በሆኑ ከተሞችና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ ትኩረት ያደረገ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ አሰራር ለመተግበር በቀጣይ ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

93.በመሆኑም የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለሆኑ ክልሎች አዳዲስ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት የሠራተኛው የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ አስመልክቶ ምክንያት ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ ጋር ተያይዘው ለሚመጡ ችግሮችን ለመከላከል ተገቢ ግንዛቤ እንዳይኖር ያደርጋል ማለትም ለአካል ጉዳት እና ለሞት ይዳረጋሉ፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ፤

94.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ሊኖራቸው ወይም በጋራ የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት በመፍጠር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

95.ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ ከማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ የሌላቸው እና በጋራ የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

96.ስለጉዳዩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

97.ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲዎች ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ከሁለቱ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲዎች ጋር በካሳ አከፋፈል ዙሪያ በጋራ ለመስራት እንዲቻል በቅርቡ በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር እና የካሳ አከፋፈል ሁኔታን አስመልክቶ ጥናት የተካሄደ በመሆኑ በጥናቱ መነሻ በማድረግ ለወደፊቱ የሚሰሩ ስራዎች መሆኑን ገልፀዋል፡፡

98. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ የሚሰሩበት አሰራር ያልተዘረጋ በመሆኑ ሠራተኞች በስራ ከሚመጡ በሽታዎች እንዴት እራሳቸውን መጠበቅና መከላከል እንዲሁም ችግሮች ሲከሰቱ በአፋጣኝ የህክምና እርዳታ የሚያገኙበት አሰራር ለማጠናከር እና በስራ ምክንያት ለአደጋዎችና በሽታዎች ሲጋለጡ አፋጣኝ የህክምና አገልግሎት ለማግኘት እንዲሁም ከመድን ዋስትና ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዳይኖራቸውና ችግሩ ሲያጋጥማቸው አፋጣኝ መልስ እንዳያገኙ ያደርጋል፡

## ትኩረት የሚሹ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች ዙሪያ ጥናትና ምርምር ማካሄድን በተመለከተ፤

99. ትኩረት የሚሹ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ማለትም ከኢትዮጲያ አሰሪዎች ፌዴሬሽን፣ ከኢትዮጲያ ሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከኢትዮጲያ ኮንስትራክሽን ህንፃ ተቋራጭ ማህበር ጋር በመቀናጀት ጥናትና ምርምር በማካሄድ የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ለማሻሻል የሚያግዝ ስልቶችን ተግባራዊ የሚደረግበት አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡

100. ይሁን እንጂ ትኩረት የሚሹ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ማለትም ከኢትዮጲያ አሰሪዎች ፌዴሬሽን፣ ከኢትዮጲያ ሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን ፣ ከኢትዮጲያ ኮንስትራክሽን ህንፃ ተቋራጭ ማህበር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከንግድ ሚኒስቴር እና ከደረጃ አውጪዎች ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶችና ምርምሮች ያልተካሄዱ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

101. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የጥናትና ምርምር ስራዎች ያልተሰሩ መሆናቸው ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት ከአቅም ውስንነት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

102. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ ትኩረት በሚሹ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች ዙሪያ ከተገለፁት አካላት ጋር በመቀናጀት የተካሄዱ ጥናትና ምርምሮች ባይኖሩም በጉዳዩ ዙሪያ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን ደረጃውን የጠበቁ አንዳንድ የፓሊሲ ጥናቶች የተካሄዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

103. በመሆኑም የሚኒስቴር መ/ቤቱ መሬት ላይ ያለውን ችግር የሚፈታ ጥናትና ምርምር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን የሚሰራበት አሰራር ባለመኖሩ በሠራተኛ የሙያ ደህንነት ዙሪያ ያሉ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ እርምጃዎች እንዳይወሰዱ ያደርጋል፡፡

## የሁለትዮሽ እና የሦስትዮሽ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤

104. የስራ ላይ አደጋዎችን እና በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን በጋራ ለመከላከል የሚያስችል የሁለትዮሽ (የአሰሪና ሰራተኛ) እና የሦስትዩሽ (ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ አሰሪና ሰራተኛ) በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

105. ይሁን እንጂ የስራ ላይ አደጋዎችን እና በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን በጋራ ለመከላከል የሚያስችል የሁለትዮሽ (የአሰሪና ሰራተኛ) እና የሦስትዩሽ (ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣አሰሪና ሰራተኛ) በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል አሰራር የተዘረጋ ቢሆንም ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

106. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በስራ ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎችና በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን በቅንጅት ከመከላከል አኳያ በሁለትዮሽ ትብብር ማለትም የህብረት ድርድር በማድረግና ስምምነት ላይ በመድረስ፣ የማኔጅመንትና የሠራተኛ ውክልና ያለው የሴፌቲ ኮሚቴ በማቋቋም የስራ ቦታ ፓሊሲ/ደንብ በመቅረጽ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑ፣ በድርጅቶች ደረጃ ደግሞ የአሠሪና ሠራተኛ አማካሪ ቦርድ እንዲሁም በአመት ሁለት ጊዜ በሚካሄድ የጋራ ጉባኤ የስራ ላይ አደጋዎችን እና በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን በቅንጅት ለመስራት የሚያስችሉ አቅጣጫዎች የሚሰጡበትና የአፈፃፀም ሂደቶች ላይ ክትትልና ግምገማ የሚደረግበት መሆኑና ይህም ችግሮችን ለመከላከል እየተደረገ ያለው ምላሽ መሆኑን ሆኖም ግን ውጤታማ አደጋ የመከላከል እና ጉዳቶችን የመቀነስ ጥረት የተጠናከረ የሁለትዮሽና የሶስትዮሽ የትብብር ስርዓት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

107. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም በኦዲት ብድኑ የአሰሪና ሠራተኛ የህብረት ስምምነት ማስረጃዎች ሲከለሱ በሠራተኞች ላይ አደጋ በሚያጋጥምበት ወቅት በመከላከል ረገድ የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ የተገለፀ ነገር ያለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፣ የጋራ ጉባኤ ሪፓርቶች ላይ በስራ ምክንያት የሚመጡ አደጋዎችና በሽታዎችን ለመከላከል በቅንጅት ለመስራት አቅጣጫዎች የተሰጡበት ሁኔታዎች ያልተቀመጡ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡እንዲሁም የአሰሪና ሠራተኛ አማካሪ ቦርድ የሚሰራው በሠራተኛውና በአሰሪው መካከል አለመግባባት በሚፈጠረበት ወቅት አለመግባባቱን ከህግ አንፃር መፍትሄ የመስጠት እና አደጋ ከደረሰ በኃላ ለሠራተኛው የሚሰጠው የካሳ ክፍያ ላይ የሚሰራ መሆኑን እንጂ አደጋ ከመድረሱ በፊት መከላከልን መሰረት ያደረጉ ስራዎች የሚሰራ አለመሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ለመረዳት የተቻለ በመሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤት የሥራ ሀላፊዎች የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አሳማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡

108. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፖርት ላይ የተሰጠ ምላሽ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት በድርጅቶች ደረጃ የሚካሄዱ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በሁለትዮሽ ትብብር የሚካሄድ ሲሆን ይህም አሰሪዎችና ሠራተኞች የህብረት ድርድር በማድረግና ስምምነት ላይ በመድረስ የስራ ላይ አደጋዎችን የመከላከል ጥረት በጋራ እንዲያካሂዱ የማኔጅመንትና የሠራተኛው ውክልና ያለው የሴፌቲ ኮሚቴ በማቋቋም የስራ ቦታ የሴፌቲ ፓሊሲ በመቅረፅ ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ መሆኑ፡፡ የሶስትዮሽ ቅንጅታዊ ትብብር በተመለከተ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ በህግ ማሻሸያ ፣ በፓሊሲ ዝግጅት እና በመመሪያ ማፅደቅ ሂደቶች ቀጥተኛ ተሳትፎ ያለው እንደመሆኑ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች በዚህ የሶስትዮሽ አካል የሚታዩ ስለሆነ በዚህ ዙሪያ ከኦዲት ቡድኑ የተሰጠው አስተያየት ተቀባይነት የሌለው መሆኑ፡፡በተጨማሪም በአመት ሁለት ጊዜ የሚካሄዱ የጋራ ጉባኤ መድረኮች በሚኒስቴር መ/ቤቱና በክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የተከናወኑ አጠቃላይ ስራዎች ቀርበው በጋራ ምክክር የሚደረግባቸውና አቅጣጫ የሚያዝባቸው እንደመሆናቸውም የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ስራዎችም በዚህ ሂደት የሚያልፍ እንጂ ከሌሎች ስራዎች ተነጥሎ የማይታይ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

109. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም በኦዲት ብድኑ የተጠቀሱትን ማስረጃ ማለትም የአሰሪና ሠራተኛ የህብረት ድርድር፣ የስራ ቦታ የሴፌቲ ፓሊሲ፣ የሶስትዮሽ ቅንጅታዊ ትስስር እና የጋራ ጉባኤ ሰነዶች በተከለሱበት ወቅት የሠራተኞች የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ለመከላከልን የሚከናወን ስራዎች በተመለከተ የቀረበ መረጃ የሌለ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

110. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ላይ ለሚደርሱ አደጋዎችና በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎች ለመከላከል የሁለትዮሽና የሶስትዮሽ ስምምነት ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት ቅድመ መከላከል ላይ በቅንጅት የሚሰሩ ባለመሆናቸው በስራ ምክንያት በሠራተኞች ላይ የሚደርሱ አደጋዎች እና በሽታዎች በጋራ ለመከላከልና ለመቀነስ እንዳይቻልያደርጋል፡፡

## 2.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከት የወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመርያዎችና አለም አቀፍ ስምምነቶችን በስራ ላይ መዋላቸውንና ውጤታማነታቸውን ለመገምገምና ለማስተካከል የሚያስችል የክትትል፣ የቁጥጥርና የግብረ መልስ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣

### በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ በአዋጅና በሌሎች ህጎች የወጡ ድንጋጌዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፤

111. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ሁኔታን፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም የስራ አካባቢን በተመለከተ በአዋጅና በሌሎች ህጎች የወጡ ድንጋጌዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና የክትትል እና ቁጥጥር ሪፖርት ግብረ መልስ ለድርጅቶች የሚላክበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

112. ይሁን እንጂ በናሙና በኦዲት ወቅት ከታዩ አስራ አንድ ድርጅቶች ሰባቱ ማለትም የኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፓሬሽን፣ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር፣ ክላሽር ፍላወር ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ፣ ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ባማኮ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር ኃላፊዎች እንደገለፁት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅና በሌሎች ህጎች የወጡ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት አሰራር ያለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

113. በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ 377/96 ንዑስ አንቀፅ 10 ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ የሚደረግ የስራ ውል ከ45 ቀናት ላልበለጠ ጊዜና ለአንድ ጊዜ ብቻ መሆን ያለበት መሆኑን ቢጠቀስም በኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት ለተወሰነ ጊዜ በሚል የተቀጠሩ ሰራተኞች ህጋዊ መብታቸው ሳይጠበቅ ወይም የቋሚ ሠራተኞችን መብት ሳያገኙ ለስምንት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ አመታት እያገለገሉ የሚገኙ መሆናቸው ይህም በስራ ምክንያት በሚከሰቱ አደጋዎችና በሽታዎች ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅምና እንክብካቤ ማግኘት ያልቻሉ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በመስክ ባካሄደው ግምገማ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡



ምስል 3፡- በኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት 15,000 ቮልት ኤሌትሪክ በመላ አካሉ የተለቀቀበትና በኤሌትሪክ የተቃጠለ ሠራተኛ

114. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የተደነገጉ የስራ ሁኔታዎች መከበራቸውን በፌደራልና በክልል ደረጃ የቁጥጥር አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ገልፀው ቁጥጥር ለተደረገላቸው ድርጅቶች ሪፓርት ተዘጋጅቶ በየአድራሻቸው የሚላክ መሆኑ፣ ሆኖም ግን የስራ ሁኔታዎች ቁጥጥር ሽፋን በሀገር ደረጃ ሲታይ 20% ያልዘለለ መሆኑን እና በየጊዜው እየጨመረ የሚሄደውን የድርጅቶች ብዛት ከማስተናገድ አኳያ የአቅም ውስንነት መኖሩን ገልፀዋል፡፡

115. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም በኦዲት ወቅት በታዩ ድርጅቶች በተለይ በኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት በ2007 ዓ.ም ሰላሳ ስምንት ጊዜያዊ እና ስልሳ ሁለት ቋሚ ሠራተኞች በስራ ደህንነትና ጤንነት ችግር የተከሰተና በስራ ላይ አደጋ የተጎዱ ሲሆን በተለይም በምሶሶ መሸከም ስራ የሚሰማሩ በርካታ ጊዜያዊ ሰራተኞች ጉዳት ካጋጠማቸው በኋላ

በአዋጁ መሠረት ማግኘት የሚገባቸውን ወርሃዊ ደሞዝ እና ተገቢውን ጥቅማ ጥቅምና ካሳ በተሟላ መልኩ እያገኙ ባለመሆናቸው የተሰጠውን መልስ አሳማኝና ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

116. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ በናሙና የታዩ ሰባት ድርጅቶች አዋጁን መሰረት በማድረግ የስራ ሁኔታዎች ቁጥጥር የተደረገባቸው ስለመሆኑ የተያያዙ ማስረጃዎች ማሳያ ሊሆኑ የሚችሉ ቢሆንም በዝርዝር የተጠቀሱትን የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ከስራ ባህሪያቸው አኳያ እንደ ሌሎች ኢንዲስትሪዎች በቅርብ ተከታትሎ የህግ ተፈፃሚነት የማረጋገጥ ስራ የተጠናከረ ያለመሆኑን ገልፀዋል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ በሚል የተቀጠሩ ሠራተኞች ህጋዊ መብት በተመለከተ የተጠቀሰው ለረዥም ጊዜ የቆየ ችግር ቢሆንም የኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ስበር ችሎት በቅፅ 3 መዝገብ ቁጥር 11924 ፣ በቅፅ 4 መዝገብ ቁጥር 225526፣ በቅፅ 4 መዝገብ ቁጥር 20885፣ በቅፅ 9 መዝገብ ቁጥር 43160 እንዲሁም በቅፅ 9 መዝገብ ቁጥር 44218 ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ በሚል በጊዜያዊነት ለረዥም ጊዜ ሲያገለግሉ የነበሩ ሠራተኞች ጉዳይ አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ እነዚህ ሠራተኞች ህጋዊ መብታቸው ለሌሎች ላልተወሰነ ጊዜ ከተቀጠሩ ሠራተኞች ጋር በእኩልነት እንዲስተናገዱ ብያኔ የተሰጠ በመሆኑ በኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት የተቀጠሩ ሠራተኞች ጉዳይ በዚህ ውሳኔ የሚስተናገድ ነው፡፡

117. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ጠቅላይ ፍርድ ስበር ችሎት ለረዥም ጊዜ ሲያገለግሉ የነበሩ ሠራተኞች ከሌሎች ህጋዊ ላልተወሰነ ጊዜ ከተቀጠሩ ሠራተኞች ጋር በእኩል እንዲስተናገዱ ብያኔ ቢሰጥም የተሰጠውን ውሳኔ ሚኒስቴር መ/ቤት ለሚደግፋቸው ድርጅቶች ባለማሳወቁ ድርጅቶችም የተሰጠውን ውሳኔ ተግባራዊ ያላደረጉ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

118. በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅና በሌሎች ህጎች የወጡ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት አሰራር የተጠናከረ ባለመሆኑ ድርጅቶች አሰሪዎች አዋጅና መመሪያዎችን ተከትለው እንዳይሰሩና የተጠያቂነት መንፈስ እንዳይኖራቸው ከማድረጉም በተጨማሪ ሰራተኞች መብትና ግዴታቸውን እንዳያውቁትና መብታቸው በአሰሪዎች እንዲጣስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መለኪያ እና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ተግባራዊ ማድረጋቸውን በተመለከተ፣

119. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክትትልና ለቁጥጥር የሚረዱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መለኪያ እና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች በመጠቀም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል::

120. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክትትልና ለቁጥጥር የሚረዱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መለኪያ እና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች የሌሉ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

121. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በየወቅቱ መኖራቸውና እነዚህም ለአዳዲስ የስራ ላይ አደጋዎችና የጤና ችግሮች እያስከተሉ መሆናቸውና እነዚህንም ችግሮች ለመቆጣጠር እና ለመቅረፍ የሚረዱ መሳሪያዎች የሌሉ መሆናቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

122. በኦሮሚያ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት መለኪያ መቆጣጠሪያ መሳሪያ በ29/10/2004 ዓ.ም በብር 3,273,010.40 (ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ሺ አስር ብር ከ አርባ ሳንቲም) ተገዝቶ ስለመሳሪያው አጠቃቀም ስልጠና ባለመሰጠቱ ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

123. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፖርት ላይ የተሰጠ ምላሽ በአቅም ውስንነት ምክንያት የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች አቅርቦትና አጠቃቀምን አስመልክቶ ያለው አገልግሎት አነስተኛ ነው፡፡

124. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክትትልና ለቁጥጥር የሚረዱ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት መለኪያ እና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች በመጠቀም ተግባራዊ ያላደረገ በመሆኑ ነባርም ሆኑ አዳዲስ የሚገቡ መሳሪያዎች በሰራተኞች ላይ ከፍተኛ የሆነ አደጋና በሽታ እያስከተሉ መሆኑንና በተጨማሪም ከፍተኛ ገንዘብ ወጥቶባቸው የሚገዙ የክትትልና የቁጥጥር መሳሪያዎች በቂ ስልጠና ተሰጥቶባቸው ወደስራ ባለመግባታቸው በሰራተኛ ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመቆጣጠርና ለመቀነስ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ አካባቢ የደረሱ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶች ያስከተሉትን ስብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች በተመለከተ፣

125. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ አካባቢ የደረሱ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶች (ከፍተኛ /ከባድ ጉዳት) ያስከተሉትን ስብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ለመገምገም እና ተመሳሳይ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ የሚያስችል የአደጋ ምርመራ / Accident investigation/ የሚያካሂድበት አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

126. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ አካባቢ የደረሱ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶች (ከፍተኛ /ከባድ ጉዳት) ያስከተሉትን ስብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ለመገምገም እና ተመሳሳይ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ የሚያስችል የአደጋ ምርመራ/Accident investigation/ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ለአብነት በኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት ድርጅት በሠራተኞች ላይ ከፍተኛና ተደጋጋሚ የሆኑ አደጋዎች በየጊዜው የሚደርሱ እና ይህም የሠራተኞች ጉዳት እያስከተለ ያለው ሰብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ከፍተኛ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

127. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በስራ ላይ የደረሱ አደጋዎች ያስከተሉትን ሰብዓዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶችን ለመገምገም እና ተመሳሳይ ጉዳቶች እንዳይከሰቱ ለመከላከል የሚያስችል የአደጋ ምርመራ/ Accident investigation/ የማካሄድ አቅም በፌደራልና በክልል ደረጃ ውስን በመሆኑ ስራው ማከናወን ያልተቻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

128. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ በስራ አካባቢ የደረሱ አደጋዎችን የመመርመር እና ቀጣይ ተመሳሳይ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ የሚያስችል አደጋን የመከላከል አቅም ለመገንባት በፌደራልና በክልል ደረጃ ያለውን ቴክኒካል እውቀትና ልምድ ውስን በመሆኑ የአደጋ ምርመራ ስርዓት የተጠናከረ ያለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

129. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ምክንያት በሠራተኞች ላይ የሚደርሱ አደጋዎች እያስከተለሉ ያለውን ሰብአዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች በመለየት ምርመራና የመከላከል ስራዎች ያልተከናወኑ በመሆኑ በስራ ላይ የሚደርሱ አደጋዎች ከመብዛታቸው በተጨማሪ ሰብዓዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች እንዲከሰቱ አስተዋፅኦ የሚያደርግ በመሆኑ በሀገር ደረጃ የችግሩን ጥልቀትና አሳሳቢነት በተጨባጭ መረጃ በመረዳት ለችግሩ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ የፖሊሲ ሀሳቦች በማመንጨት ለተግባር ለማዋል አያስችልም፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ዘርፍን ያገናዘበ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መመዘኛ መስፈርት/ ስታንዳርድ/ አዘጋጅቶ ማሰራጨቱን በተመለከተ፤

130. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ዘርፍን(ለምሳሌ ኮንስትራክሽን፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ እርሻ፣ ወዘተ) ያገናዘበ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መመዘኛ መስፈርት/ ስታንዳርድ/ አዘጋጅቶ ለድርጅቶች ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

131. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በናሙና የተመረጡ አስራ አንድ ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጲያ የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፓሬሽን እና ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ ፡የኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት፣ብሄራዊ ትምባሆ አክሲዮን ማህበር ፣ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ባማኮ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ፣ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር፣ክሎቨር ፍላወር ኃ/ የተ/ የግል ማህበር፣ ዛምራ ኮንስትራክሽ ኃ/የተ/የግል ማህበር የሙያ ዘርፉን ያገናዘበ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መመዘኛ መስፈርት/ስታንዳርድ/ ያልደረሳቸው መሆኑን በኦዲት ወቅት ገልፀዋል፡፡

132. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች ቃለ መጠይቅ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ መልስ የሌለ መሆኑ፡፡

133. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን የእርሻ ዘርፍ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት መመሪያ በ1999 ዓ.ም አውጥቶ ለሚመለከታቸው አካላት በማሰራጨት ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኙ መሆኑን፡፡ እነዚህ ስታንዳርዶች ተፈፃሚ በማድረግ ረገድ የፌደራልና የክልል የስራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች ኃላፊነት የተሰጣቸው መሆኑ በህጉ የተመለከቱ ሲሆን የኢትዮጲያ የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን እና ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ ፡የኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት፣ብሄራዊ ትምባሆ አክሲዮን ማህበር ፣ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ባማኮ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ፣ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር፣ክሌቨር ፍላወር ኃ/ የተ/ የግል ማህበር፣ ዛምራ ኮንስትራክሽ ኃ/የተ/የግል ማህበር ተግባራዊ ማድረግ የሚገባቸው መሆኑ፡፡

134. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም በኦዲት ብድኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙ.ያ ዘርፉን ያገናዘበ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት መመዘኛ መስፍርት ለድርጅቶች ስለማሰራጨታቸው የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ ድርጅቶች መመዘኛ መስፍርቱ ሳይደረሳቸው ተግባራዊ ማድረግ የማይችሉ በመሆኑ የተሰጠው መልስ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

135. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙ.ያ ዘርፉ(ለምሳሌ ኮንስትራክሽን፣ ማኒፋክቸሪንግ፣ እርሻ፣ ወዘተ)ያገናዘበ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት መመዘኛ መስፈርት/ ስታንዳርድ/ አዘጋጅቶ ለድርጅቶች ባለማሰራጨቱ ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው ስራዎች መስፈርቶችን መሰረት አድርገው እንዳይሰሩ እና ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖር አድርጓል፡፡

## በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከተ የመረጃ ቋት (Data base) መኖሩን በተመለከተ፤

136. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገር አቀፍ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ፣ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከተ እንዲሁም በዚህ ዙሪያ የተከሰቱ አደጋዎችንና ክስተቶችን የሚይዝበት የመረጃ አያያዝ ስርዓት ወይም መረጃ ቋት (Data base) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

137. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገር አቀፍ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የመረጃ ቋጥ የሌለው መሆኑ፣ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነትን በተመለከተ እንዲሁም በዚህ ዙሪያ የተከሰቱ አደጋዎችንና ክስተቶችን የሚይዝበት የመረጃ አያያዝ ስርዓት ወይም መረጃ ቋት (Data base) ያልተዘጋጀ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፣ በዚህም ምክንያት ድጋፍና ክትትል ከሚያደረግላቸው ድርጅቶችና ክልሎች የአደጋ ሪፓርት የላከና ያላከውን ድርጅት በቀላሉ ለመለየት ያልተቻለ መሆኑ እንዲሁም አንድ ድርጅት በደረሰ አደጋ ሌላው ድርጅት

የሚማርበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ያላደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

138. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ድርጅቶች በስራ ላይ የሚከሰቱ አደጋዎችን በየደረጃው ባሉ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ አስፈፃሚ አካላት በየወቅቱ ሪፓርት የማያደረጉ መሆኑ እና  የኢንሹራንስና የማህበራዊ ዋስትና ተቋማት ድርጅቶች በገቡላቸው ውል መሰረት የሚከሰቱ አደጋዎችን ሪፓርት የማያደረጉ መሆኑ ይህም በሀገሪቱ የተሟላ የስራ ላይ አደጋና የጤና ጉዳት መረጃዎች (ዳታ ቤዝ) እንዳይፈጠር ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

139. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ አሰፈፃሚ አካላትም ሆነ ከኢንሹራንስና የማህበራዊ ዋስትና ተቋማት የአደጋ ሪፓርት በተጠናከረ መልኩ የሚላክበት እና የተሟላ የስራ ላይ አደጋና የጤና ጉዳት መረጃዎች (ዳታ ቤዝ) የሚያዝበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባውን በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

140. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ የሙያ ደህንነትና ጤንነት የመረጃ ስርዓት በተመለከተ በሀገሪቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ ሪፓርት የሚያደረጉ የስራ ላይ አደጋዎችን የጤና ጉዳት መረጃዎችን እጅግ ውስን በመሆናቸው ሀገራዊ ገፅታን የሚያሳይ ባይሆንም የተገኙ መረጃዎችንም ቢሆን በማጠናቀር ሰነድ ተዘጋጅቶ ለድርጅቶች የሚሰራጭ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

141. በመሆኑም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሰሪና የሠራተኛ ጉዳይ የሚመለከቱ መረጃዎች በመረጃ ቋት ተደራጅተው ያልተቀመጡ እንዲሁም የስራ ላይ አደጋና የጤና ጉዳት መረጃዎች በየጊዜው በተደራጀ መልክ የሚያዙ ባለመሆናቸው በአሰሪና ሰራተኛ ዙሪያ ያሉ መረጃዎች እንዳይጠናቀሩ እና በዘርፉ እየተከሰቱና እያጋጠሙ ያሉ ችግሮች እንዳይለዩና የመፍትሄ እርምጃዎች ተጨባጭ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ እንዳይወሰድባቸው አድርጓል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራልና በክልል የሚገኙ ድርጅቶችን ዝርዝር መረጃ መያዝ በተመለከተ፤

142. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራልና በክልል የሚገኙ ድርጅቶችን ዝርዝር መረጃ ሊይዝ ይገባል፣

143. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራልና በክልል የሚገኙ ድርጅቶችን ዝርዝር መረጃ የሚይዝበት አሰራር ያለመኖሩን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

144. በተመሳሳይ መልኩ በናሙና ከተመረጡ ሶስት ክልሎች ማለትም አዲስ አበባ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ኦሮሚያ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና ደቡብ ክልል ሠራተኛና

ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ድጋፍ የሚያደረጉላቸውን ድርጅቶች ዝርዝር መረጃ የሚይዙበት አሰራር የሌላቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

145. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ በፌደራል ሆነ በክልል ደረጃ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሚሸፈኑ ድርጅቶችን ዝርዝር የያዘ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የተጠናከረ ስርዓት ባለመኖሩ መረጃው በተሟላ ሁኔታ ያልተያዘ ቢሆንም ለወደፊቱ በፓሊሲው በመታገዝ ስርዓት እንዲዘረጋ የሚያደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

146. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ምላሽ አልሰጡበትም፡፡

147. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራልና በክልል ደረጃ የሚገኙ ድርጅቶችን ዝርዝር መረጃ የሚይዝበት አሰራር ያልዘረጋ በመሆኑ በሀገር ደረጃ ምን ያህል ድርጅቶች እና ምን ያህል ሠራተኞች እንዲሁም በምን ደረጃ ላይ ድርጅቶች እንደሚገኙ እንዳይታወቅ አድርጓል፡፡

## የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በተመለከተ የቅሬታ አቀራረብን በተመለከተ፤

148. የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በተመለከተ ከደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትና መረጃዎች ተጠናቅረው የሚያዙበት አሰራር ስረዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

149. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በተመለከተ ከሠራተኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎች በአግባቡ የሚስተናገዱበትና መረጃዎችም ተጠናቅረው የሚቀርቡበት አሰራር ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት አልቀረበም፡፡

150. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በተመለከተ ከደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመለየት መረጃ የመያዝና በጥናት ላይ ተመስርቶ ለቅሬታዎቹ መፍትሄ የመስጠት አሰራር ከስራ ሂደቱና ሌሎች ቡድኖች ጋር በጋራ በመሆን የተገልጋይ እርካታ ጥናት የተዘጋጀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

151. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የተገልጋይ እርካታ ጥናት ቢኖርም የቅሬታ ሰሚ አካል ያለመኖሩ (ክፍሉ የሰው ኃይል የሌለው መሆኑ) እንዲሁም የቀረቡ ቅሬታዎችና የተሰጡ መፍትሄዎችን የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

152. ሚኒስቴር መ//ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፓርት ላይ የተሰጠ ምላሽ አገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ ተገልጋዩ ቅሬታውን የሚገለፅበት ከላይ እስከታች የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት

በመ/ቤቱ ውስጥ ያለ ስለሆነ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮችም በዚህ ስርዓት መሰረት የሚስተናገዱ እንጂ ተነጥለው የሚታዩ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

153. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የኦዲት ቡድኑ መረጃ በከለሰበት ወቅት በሙያ ደህንነትና ጤንነት ቡድን የቀረቡ ቅሬታዎች የሚያሳይ መረጃ በመ/ቤቱ ባለመቅረቡ ምክንያት የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

154. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነትን በተመለከተ ከተገልጋይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በአግባቡ የሚያስተናግድበት እና ለሚነሱ ቅሬታዎች አፋጣኝ መልስ የሚሰጥበት አሰራር ባለመኖሩ ከሠራተኞች የሚነሱ ቅሬታዎች በወቅቱ መፍታሄ እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

## በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ግንዛቤ የሚያዳብሩ ለምሳሌ ፓስተሮች፣ ብሮሸሮች እና ሌሎችም የሚሰራጭበት አሰራር መኖሩን በተመለከተ፤

155. በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ግንዛቤ የሚያዳብሩ ፓስተሮች፣ ብሮሸሮችና/ በህትመትና በኤሌትሮኒክስ ዘዴ ሊዘጋጁ፣ ሊሰራጩ እና ሊተዋወቁ ይገባል፡፡

156. ይሁን እንጂ በናሙና ከተወሰዱ አስራ አንድ ድርድቶች ውስጥ አስሩ ማለትም የኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት፣ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክሽን ኮርፓሬሽን፣ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ የኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት፣ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር፣ ተክለብርሃን አምባዬ ካንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ባማኮ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ዛምራ ካንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ ክሌበር ፍላወር ኃ/የተ/የግል ማህበር ለመረዳት እንደተቻለው በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ግንዛቤ የሚያዳብሩ ፓስተሮች፣ ብሮሸሮችና/ በኤሌትሮኒክስ ዘዴ የሚዘጋጅበት አሰራር ቢኖርም እንዲሰራጭ እና እንዲያውቁ ያላደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለመጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፣

157. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በህግ ከተሰጠው ተልዕኮ አንዱ የሆነውን የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ በተመለከተ ግንዛቤ የሚያዳብሩ መረጃዎችን በኢትዮጲያ ሬድዮ ማህበራዊ ቅኝት በሚል ፕሮግራም በሳምንት ሁለት ጊዜ የ46 ደቂቃ የአየር ጊዜ በመግዛት ትምህርታዊ መልዕክቶቹን ለህዝብ ተደራሽ ያደረጉ መሆኑን ከዚህም በተጨማሪ አዲስ ምዕራፍ በሚል ስያሜ በአመት አራት ጊዜ የሚታተምና የሚሰራጭ የሚኒስቴር መ/ቤቱ መፅሄት ላይ የሙያ ደህንነትና ጤንነት የሚመለከቱ ትምህርታዊ ፁሁፎችን በየጊዜው የሚወጡበትና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር መኖሩን ገልፀዋል፡፡

158. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም በናሙና ከተመረጡ ድርጅቶች ለመረዳት እንደተቻለው ፖስተሮች፣ ብሮሸሮች ወዘተ የማይደርሳቸውና እንዲያውቁት ያልተደረገ መሆኑን የገለፁ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

159. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኦዲት ቡድኑ በረቂቅ ሪፖርት ላይ የተሰጠ ምላሽ የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከተ የተመለከቱ ማስታወቂያዎች ( ፓስተሮች፣ ብሮሸሮች እና በራሪ ምልክቶች) በተለያዩ የሴፌቲ ጉዳዮች ዙሪያ የተዘጋጁ፣ የታተሙና ለድርጅቶችም ያሰራጨ መሆኑን ነገር ግን በህትመት ውስንነት ምክንያት ለሁሉም ድርጅቶች የሴፌቲ ፓስተሮችን የማሰራጨት ሁኔታ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

160. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ግንዛቤ የሚያዳብሩ ፓስተሮች፣ ብሮሸሮችና የመሳሰሉትን በማዘጋጀት በሁሉም ድርጅቶች በበቂ ሁኔታ በማሰራጨት እንዲያውቁ ባለመደረጉ ሠራተኞች በሚሰሩት ስራ ደህንነታቸውንና ጤንነታቸውን እንዴት መጠበቅና ከአደጋና በሽታ እራሳቸውን እንዴት መከላከል እንዳለባቸው በቂ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

161. የኦዲት ሪፓርቱን አስመልክቶ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች እንደገለፁት በአጠቃላይ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያካሄደው የክዋኔ ኦዲት የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎትን ለማሻሻል እና በህግ የተደነገጉ ሁኔዎችን ይበልጥ ተፈፃሚ ከማድረግ አኳያ ጠቃሚ ግብአቶች የተገኙበትና ውጤቱም ለመ/ቤቶችን ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑ የሚታመንበት ቢሆንም የስራ ዘርፉ ከሚጠይቀው እውቀትና ክህሎት እንዲሁም ዘመናዊ የሆኑ እቃዎችና መሳሪያዎች አቅርቦት አንፃር የስለጠነ ባለሙያ የማግኘት እጥረት ከመኖሩም ባሻገር በከፍተኛ ደረጃ የሰራተኛ ፍልሰት በመኖሩ እንዲሁም ለሰራው የሚያስፈልጉ እቃዎችና መሳሪያዎች ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ በመሆኑ መ/ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ያለው የአቅም ውስንነት ከግምት ውስጥ ያለበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያዎ

## 3.1 የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በመከላከል መርህ ላይ ተመስርቶ በስራ ቦታዎች የሚተገበርበት እና በስራ ላይ አደጋዎች ሲከሰቱ ተገቢውን የሆነ የመልሶ ማቋቋም ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

162. ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ድርጅቶች እንዲያቋቁሙ የሚያደርጉ እና ባላቋቋሙ ድርጅቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር የማያደርጉ መሆኑ፣

163. በሚኒስቴር መ/ቤቱና በክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አሰሪዎች የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ልብስና ሌሎች ቁሳቀሶችን ለሠራተኞቻቸው የማያቀርቡ መኖራቸውና ይህንንም ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ያልተዘረጋ መሆኑ፤

164. አሰሪዎች የስራ ቦታና ግቢ የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ስራዎች በሚከናወኑባቸው ቦታዎች ላይ ሊለጠፉ የሚገባቸው ማስታወቂያዎች የማይለጠፉ መሆናቸው ይህንንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ያልዘረጋ መሆኑ፤

165. አዳዲስ መሳሪያዎች ሲተከሉ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው ምርመራ የማይደረግባቸው መሆኑ ይህንንም ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች በየወቅቱ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ያልዘረጋ መሆኑ፤

166. ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት ድርጅት የሚገኙ ማንኛውንም ነገር ማለትም ጥሬ እቃዎች፣ የሚመረቱ ምርቶች በመጠኑ (sampling) ወስደው በሠራተኞች ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆኑን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የተሰሩ ስራዎች ስለመኖራቸው ማስረጃ ያልተገኘ መሆኑ፣

167. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም በስራ አካባቢ ጥበቃ ላይ ምርጥ ተመክሮዎችን የመለየት፣ የመቀመር እንዲሁም የማስፋፋት ስራዎችን ያላከናወነ መሆኑ፣

168. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት የቴክኒክ ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ለክልል

ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ያላሰራጩ መሆኑ፣

169. በድርጅቶች ውስጥ የሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት የሚጎዱ ሁኔታዎች ሲከሰቱ እና የሚደርሰውን ማንኛውም አደጋ እና በሽታዎች አሰሪዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ለክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የሚያሳውቁበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

170. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር መመሪያ የያዘ ሠንጠረዥ ለድርጅቶች እንዲሰራጭ ያላደረገ እና በየአምስት ዓመቱ እንዲሻሻል ያላደረገ መሆኑ፤

171. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ልዩ ድጋፍ በሚሹና የኢንቨስትመንት መዳረሻ በሆኑ ክልሎች በሠራተኛ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ የሚሰጠውን እገዛ የመለየት ስራዎች የተከናወኑ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

172. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ የስራ ዘርፎች ክፍተቶችን በመለየት ሠራተኞች የሚሰሩት ስራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋ እንዲሁም በጤና ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ የሚያስፈልጉ ጥንቃቄዎች እና እርምጃዎች በተመለከተ በተግባር የተደገፈ ስልጠና የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

## 3.2 <u>የስራ ላይ አደጋዎችን እና በሥራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቅንጅታዊ አሰራር የተዘረጋ እና በዘርፉ የሚያጋጥሙ የስራ ላይ አደጋዎች፣ የጤና ችግሮች የሚያስፈልጉ የሚሰበሰቡ የሚደራጁና የሚሰራጩበት ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋናውጤታማ መገምገም፣</u>

173. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ጋር የተጠናከረ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ የሌላቸው እና በጋራ የሚሰሩበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤

174. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትኩረት የሚሹ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ማለትም ከኢትዮጲያ አሰሪዎች ማህበር ኮንፌዴሬሽን፣ከኢትዮጲያ ሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን፣ ከኢትዮጲያ አበባ፣ ከኢትዮጲያ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ ማህበር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ፣ ከንግድ ሚኒስቴር እና ከደረጃ አውጪዎች ጋር በመቀናጀት ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶችና ምርምሮች ያላካሄደ መሆኑ፤

175. የስራ ላይ አደጋዎችን እና በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን በጋራ ለመከላከል የሚያስችል የሁለትዮሽ (የአሰሪና ሰራተኛ) እና የሦስትዩሽ (ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣አሰሪና ሰራተኛ) በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል አሰራር ስርዓት ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚያሳይ

ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

## 3.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከት የወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመርያዎችና አለም አቀፍ ስምምነቶችን በስራ ላይ መዋላቸውንና ውጤታማነታቸውን ለመገምገምና ለማስተካከል የሚያስችል የክትትል፣ የቁጥጥርና የግብረ መልስ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣

176. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅና በሌሎች ህጎች የወጡ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት አሰራር የተጠናከረ አለመሆኑ፤

177. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክትትልና ለቁጥጥር የሚረዱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መለኪያ እና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች የሌለው መሆኑ፣

178. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ አካባቢ የደረሱ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶች (ከፍተኛ /ከባድ ጉዳት) ያስከተሉትን ሰብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ለመገምገም እና ተመሳሳይ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ የሚያስችል የአደጋ ምርመራ/Accident investigation/ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

179. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ዘርፍን ያገናዘበ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መመዘኛ መስፈርት/ስታንዳርድ/ ያዘጋጀ ቢሆንም ለድርጅቶች እንዲሰራጭ ያላደረገ መሆኑ፤

180. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ላይ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶችን ከመከላከል አኳያ የመድን ዋስትና ሰጪ ተቋማትን በማስተማር የትብብርና የቅንጅት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

181. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገር አቀፍ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የመረጃ ቋጥ የሌለው መሆኑ፣የሙያ ደህንነትና ጤንነትን በተመለከተ እንዲሁም በዚህ ዙሪያ የተከሰቱ አደጋዎችንና ክስተቶችን የሚይዝበት የመረጃ አያያዝ ስርዓት ወይም መረጃ ቋት (Data base) የሌለው መሆኑ፣

182. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራልና በክልል የሚገኙ ድርጅቶችን ዝርዝር መረጃ የሚይዝበት አሰራር የሌለ መሆኑ፣

183. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በተመለከተ ከሠራተኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎች በአግባቡ የሚስተናገዱበትና መረጃዎችም ተጠናቅረው የሚቀርቡበት አሰራር የሌለ መሆኑ፣

184. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ግንዛቤ የሚያዳብሩ ፓስተሮች፣ ብሮሸሮችና/ በኤሌትሮኒክስ ዘዴ እንዲሰራጭ እና እንዲያውቁ ያልተደረገ መሆኑ፣

በአጠቃላይ በሀገሪቱ የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከወን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች በስራ ላይ እያሉ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን እና በሽታዎችን ለማስወገድ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በመከላከል መርህ ላይ ተመስርቶ በስራ ቦታዎች የሚተገበሩበት የአሰራር ስርዓት በመዘረጋት ድርጅቶች ለሠራተኞች የአደጋ መከላከያ አልባሳትና ሌሎች ቁሳቁሶች እንዲያቀርቡና ስለአጠቃቀማቸው መመሪያ በመስጠት፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ያሉ ክፍተቶች በመለየት ለሠራተኞችና ለአሰሪዎች ስልጠና የሚሰጥበት እና ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎች በስፋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማለትም ከኢትዮጲያ ሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን፣ ከኢትዮጲያ አሰሪዎች ፌዴሬሽን እና የክልል አሰፈፃሚ አካላት እንዲሁም ከአሰሪዎች ጋር በመቀናጀትና በማስተባበር የሠራተኛው ደህንነት እንዲጠበቅ መደረግ አለበት፡፡ አሰሪዎች ለሠራተኞች ሟሟላት ያላባቸውን በአዋጅ 377/96 የተገለፁ ጉዳዮች መሟላታቸውን እና በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን እንዲሁም ተግባራዊነቱን የሚያረጋግጥ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ባለመዘርጋቱ ምክንያት ሠራተኞች በስራ ላይ በሚያጋጥማቸው አደጋ ለአካል ጉዳትና ለሞት ተጋልጠዋል፡፡ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ያሻሽላሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሀሳብ

## 4.1 በሥራ ቦታዎች የሚከሰቱ አደጋዎች እና የጤና ችግሮችን ለመከላከል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤

185. ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ድርጅቶች እንዲያቋቁሙ እና ባላቋቋሙ ድርጅቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

186. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አሰሪዎች የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ልብስና ሌሎች ቁሳቀሶችን ለሠራተኞቻቸው እንዲያሟሉ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በማያሟሉ ድርጅቶች ላይ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

187. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አሰሪዎች የስራ ቦታና ግቢ የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ስራዎች በሚከናወኑባቸው ቦታዎች ላይ ሊለጠፉ የሚገባቸው ማስታወቂያዎች መለጠፋቸውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ይህንን በማይፈፅሙ ድርጅቶች ላይ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

188. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አሰሪዎች አዳዲስ መሳሪያዎች ሲተክሉ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው ምርመራ የተደረገባቸው ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

189. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት ድርጅት የሚገኙ ማንኛውንም ነገር ማለትም ጥሬ እቃዎች፣ የሚመረቱ ምርቶች በመጠኑ (sampling) ወስደው በሠራተኞች ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆኑን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

190. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም በስራ አካባቢ ጥበቃ ላይ ምርጥ ተመክሮዎችን የሚለይበት የሚቀምርበትና እንዲሁም የሚያስፋፋበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

191. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት የቴክኒክ ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ለክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ሊያሰራጭ እና ልዩ ድጋፍ በሚሹና የኢንቨስትመንት

መዳረሻ በሆኑ ክልሎች በሠራተኛ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ የሚሰጠውን እገዛ በመለየት ድጋፍ የሚሰጥበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

192. በድርጅቶች ውስጥ የሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት የሚጎዱ ሁኔታዎች ሲከሰቱ እና የሚደርሰውን ማንኛውም አደጋ እና በሽታዎች አሰሪዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ለክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የሚያሳውቁበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

193. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር መመሪያ ሊያዘጋጅና ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ እንዲሁም በየአምስት ዓመቱ መመሪያውን ሊያሻሽል ይገባል፡፡

194. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ የስራ ዘርፎች ክፍተቶችን በመለየት ሠራተኞች የሚሰሩት ስራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋ እንዲሁም በጤና ላይ የሚደርስ ጉዳትንለማስወገድ የሚያስፈልጉ ጥንቃቄዎች እና እርምጃዎች በተመለከተ በተግባር የተደገፈ ስልጠና የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

## 4.2 የስራ ላይ አደጋዎችን እና በሥራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቅንጅታዊ አሰራር የተዘረጋ እና በዘርፉ የሚያጋጥሙ የስራ ላይ አደጋዎች፣ የጤና ችግሮች የሚያስፈልጉ ፣ የሚሰበሰቡበት፣ የሚደራጁና የሚሰራጩበት ኢኮኖሚያዊ ፣ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤

195. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ጋር የተጠናከረ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

196. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትኩረት የሚሹ የሙ.ያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ማለትም ከኢትዮጲያ አሰሪዎች ማህበር ኮንፌዴሬሽን፣ከኢትዮጲያ ሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን፣ ከኢትዮጲያ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭ ማህበር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከንግድ ሚኒስቴር እና ከደረጃ አውጪዎች ጋር በመቀናጀት ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶችና ምርምሮችን ሊያካሂድ ይገባል፡፡

197. የስራ ላይ አደጋዎችን እና በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን በጋራ ለመከላከል የሚያስችል የሁለትዮሽ (የአሰሪና ሰራተኛ) እና የሦስትዮሽ (ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣አሰሪና ሰራተኛ) ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

## 4.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከት የወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመርያዎችና አለም አቀፍ ስምምነቶችን በስራ ላይ መዋላቸውንና ውጤታማነታቸውን ለመገምገምና ለማስተካከል የሚያስችል የክትትል፣ የቁጥጥርና የግብረ መልስ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣

198. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅና በሌሎች ህጎች የወጡ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት አሰራር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

199. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክትትልና ለቁጥጥር የሚረዱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መለኪያ እና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች በማሟላት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

200. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ አካባቢ የደረሱ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶች (ከፍተኛ /ከባድ ጉዳት) ያስከተሉትን ሰብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ለመገምገም እና ተመሳሳይ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ የሚያስችል የአደጋ ምርመራ/Accident investigation/ **የአሰራር** ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

201. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ዘርፍን ያገናዘበ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መመዘኛ መስፈርት/ስታንዳርድ/ ለድርጅቶች እንዲሰራጭ ሊያደርግ ይገባል፡፡

202. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ላይ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶችን ከመከላከል አኳያ የመድን ዋስትና ሰጪ ተቋማትን በማስተማር የትብብርና የቅንጅት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

203. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገር አቀፍ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ መረጃዎችን፣ በፌደራልና በክልል የሚገኙ ድርጅቶችን ዝርዝር፣ ሰራተኞች ላይ በስራ ምክንያት የተከሰቱ አደጋዎችንና ክስተቶችን እና ሌሎችንም ተያያዥ መረጃዎችን አጠናቅሮ የሚይዝበት የመረጃ ቋት(Data base) ሊኖረው ይገባል፡፡

204. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሠራተኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎች በአግባቡ የሚያስተናግድበትና መረጃዎችንም አጠናቅሮ የሚይዝበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በሀገሪቱ የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲካሄድ ለማድረግ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና በዘርፉ የወጡ አለም አቀፍ ስምምነቶች ጥናቶች መሰረት በማድረግ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግና አፈፃፀማቸውን ለመከታተል የተጠናከረ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ለመዘረጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌደራልና የክልል አሰፈፃሚ አካላት እንዲሁም የአሰሪዎችን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ይህንን ለማሳካት በፌደራልና በክልል የሚገኙ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በዚህም ሪፓርት የተገለፁት ግኝቶች፣ መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሀሳቦች በቀጥታ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሙሉ በሙሉ የሚሰራውና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በቅንጅት የሚሰራው ቢሆኑም፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠው ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ለሚመለከተው መ/ቤት በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም የሠራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊዎች፣ የመንግስት እና የግል አሰሪዎች(ድርጅቶች) እና ሠራተኞች እንዲሁም ማህበራት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) አባሪ 1

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ:- **የሠራተኞች የሙ-ያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የአሰራር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተካሄደ መሆኑን መገምገም፤**

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት:-**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር**

| **የኦዲት ጭብጥ** | **የኦዲት ንዑስ ጭብጥ** (Sub-Issues) | **የመገምገሚያ መስፈርት** (Evaluative criteria) |
|---|---|---|
| 1. በስራ ላይ አደጋዎችን እና በስራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን በሽታዎችን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ የአሰራር ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤ | 1.1.የሙ-ያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በመከላከል መርህ ላይ ተመስርቶ በስራ ቦታዎች የሚተገበርበት ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ሰርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣ | 1.1.1 ሠራተኞች የሚሰሩት ስራ ሊሚያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋ እንዲሁም በጤና ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ የሚያስፈልገውን ጥንቃቄዎች እና እርምጃዎች በተመለከተ ስልጠና ያሉትን ክፍተቶች በመለየት በተግባር የተደገፉ ስልጠና የሚሰጥበት አሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል<br>(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ ገፅ 96) |
| | | 1.1.2.አሰሪዎች የሙ-ያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ በተቋማቸው ሊያቋቁሙ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ ገፅ 96) |
| | | 1.1.3 ድርጅቶች ለሰራተኞች የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ልብስና ሌሎች ቁሳቁሶችን ሊያቀርቡና ስለአጠቃቀሙ መመሪያ(ስልጠና)ሊሰጡ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ ገፅ 96) |
| | | 1.1.4 የድርጅቶች የስራ ቦታና ግቢ የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑ ሊረጋገጥ እና ሊለጠፍ የሚገባቸውን ማስታወቂያዎችሊለጥፉይገባል፡፡<br>(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ ገፅ 96)) |
| | | 1.1.5. አዳዲስ ድርጅቶች ሲሰሩ፣ያሉት ነባር ድርጅቶች ሲሰፉና ሲለወጡ ወይም መሳሪያዎች ሲተከሉ በሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት ጉዳት የማያደርስ መሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ:- የስላማዊ ኢንዲስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 11) |
| | | 1.1.6 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት |

| | | |
|---|---|---|
| | | ድርጅቶችየሚገኙማንኛውንምነገርማለትምጥሬእቃዎች፣የሚመረቱምርቶች በመጠኑ(sampling) ወስደው በሰራተኞች ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ምርመራ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 12) |
| | | 1.1.7 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም በስራ አካባቢ ጥበቃ ላይ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየት ሊቀምርና ሊያስፋፋ እውቅና ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 2) |
| | | 1.1.8 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችን በመለየትስልጠናዎችንየሚሰጥበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ ገፅ 1) |
| | | 1.1.9 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት የቴክኒክ ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ሊያዘጋጅና ሊያሰራጭ እንዲሁም ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ ገፅ 2) |
| | 1.2የስራ ላይ አደጋዎችን በሽታዎችን በአምራቹ የስው ኃይልና በኢኮኖሚ እድገት ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽዕኖን ለመከላከልና ለማስወገድ እንዲሁም ችግሩ ሲከሰት ተገቢ የሆኑ የህክምና ፣የጉዳት ካሳ እና የመልሶ ማቋቋም ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣ | 1.2.1 በድርጅቱ መሳሪያዎች ላይ የሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት የሚጎዳ ሁኔታዎች ሲገኙ እና የሚደርሰው ማንኛውም አደጋ ሠራተኞች የሚያሳውቁበት የአሰራር ስርዕት ሊዘረጋ ይገባል፣ ያልገባ፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ ገፅ 98) |
| | | 1.2.2 በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችና አደጋዎች ሊመዘገቡ ይገባል፡፡<br><br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ ገፅ 98) |
| | | 1.2.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካለው ባለስልጣን ጋር በመመካከር በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ዝርዝር መመሪያ የያዘ ሰንጠረዥ ሊያዘጋጅና ሊያሰራጭ እንዲሁም በየአምስት አመቱ ሊያሻሽል<br><br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ ገፅ 105) |

| | | |
|---|---|---|
| | | 1.2.4 ድርጅቶች የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና መስጫ መሳሪያ ሊኖራቸውና የሠራተኛ ጉዳት በሚያጋጥም ወቅት የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ በጊዜ ሊሰጡ እና ተስማሚ በሆነ የመጓጓዥ ዘዴ በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው የህክምና ጣቢያ ሊያደርሰው ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ ገፅ 105) |
| | | 1.2.5 ሰራተኞች በስራ ላይ ጉዳት ሲያጋትማቸው ድርጅቶች የጉዳት ካሳ የሚከፈልበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ የወጣ አዋጅ ገፅ 117) |
| 2. የስራ ላይ አደጋዎችን እና በስራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ቅንጅታዊ አሰራር የተዘረጋ እና በዘርፉ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የሚበሰቡበት የሚደራጁበትና የሚሰራበት ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋ ውጤታማ የመረጃ አያያዝ ፤ | 2.1 በስራ ቦታዎች የሚከሰቱ አደጋዎች እና የጤና ችግሮች ለመከላከል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን አስተባብሮና አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋቱን እና ተግባራዊ የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም ፤ | 2.1.1ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማለትም (የሠራተኛና የአሰሪዎች ማህበር፣ ማህበራዊ ዋስትና የኢንሹራንስ ተቋማት፣ከፍተኛ ትምህርት፣የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና የምርምር ተቋማት) በመሆን በቅንጅት የሚሰራበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡<br>(ምንጭ፡- የስላማዊ ኢንዲስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 1) |
| | | 2.1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የድርጅቶችን አገልግሎት በተመለከተ በፌደራልና በክልል ደረጃ የልምድ ልውውጥ፣ የትብብርና የቅንጅት መድረኮችን ሊያስተባብር እና አፈፃፀሙን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>የስላማዊ ኢንዲስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 2) |
| | | 2.1.3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ልዩ ድጋፍ በሚሹና የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለሆኑ ክልሎች በሠራተኛ ሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ የሚሰጠውን እገዛ በመለየት ሊገመገም እና ስለተግባራዊነቱ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፤<br>(ምንጭ፡- የስላማዊ ኢንዲስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 3) |
| | | 2.1.4 ሚ/ር መ/ቤቱ በሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ከጤና ጥበቃ ሚ/ር እና ከማህበራዊ ዋስትና (ኤጀንሲ) ጋር የተጠናከረ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ሊኖራቸው ወይም በጋራ የሚሰሩበት አሰራር ስርዓት በመፍጠር |


| | | |
|---|---|---|
| | | ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፣<br>(ምንጭ፡- ብሄራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፓሊሲና ስትራቴጂይ ገፅ 9) |
| | | 2.1.5 ትኩረት የሚሹ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው ማለትም ከአሰሪዎች፣ ከሠራተኞች፣ ከጤና ሚኒስቴር፣ ከዩንቨርሲቲዎች፣ ከንግድ ሚኒስቴር እና ከደረጃ አውጪዎች ጋር በመቀናጀት ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- ብሄራዊየሙያ ደህንነትና ጤንነት ፓሊሲና ስትራቴጂይ ገፅ 12) |
| | | 2.1.6 የስራ ላይ አደጋዎችን እና በስራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን በጋራ ለመከላከል የሚያስችል የሁለትዮሽ (የአሰሪና ሰራተኛ)፣የሦስትዩሽ ( ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣አሰሪና ሰራተኛ ) እና የሌሎች የባለድርሻ አካላት ትብብርና ቅንጅት ተግባራዊነት ሊጠናከር ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- ብሄራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፓሊሲና ስትራቴጂይ ገፅ 8) |
| | | 2.1.7 የስራ ላይ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶችን ከመከላከል አኳያ ከመድን ዋስትና ስጪ ተቋማት በማስተማር የትብብርና የቅንጅት ስርዓት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- ብሄራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፓሊሲና ስትራቴጂይ ገፅ 8) |
| | 2.2 በስራ ቦታዎች ሰለሚከሰቱ አደጋዎችና ለጤና ችግሮች በነዚህ ምክንያት የተከሰቱ የሀብት ብክነትና የንብረት ውድመት እንዲሁም የስራ ላይ አደጎችንና ጉዳቶችን ለመከላለል የተወሰዱ እርምጃዎች በሚመለከት መረጃዎችን በመሰብሰብ በማደራጀትና በመተንተን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የሚደረግበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉ መገምገም፣ | 2.2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከተ እንዲሁም በዚህ ዙሪያ የተከሰቱ አደጋዎችንና ክስተቶችን የሚይዝበት የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋ እና መረጃዎቹን በማጠናቀር በመተንተንና በማጀራጀት ለሚመለከተው አካል ሊያስተላልፍና በራሱ የአያያዝ ስርዓት ወይም ዳታ ቤዝ ሊይዝ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 3) |
| | | 2.2.2 በስራ ቦታ ትብብርና ማህበራዊ ምክክር ስርዓት አፈፃፀም እና መሰል ጥናቶች ዙሪያ የሚያጋጥሙ የአፈፃፀም ክፍተቶችን በጥናት በመለየት የተሰበሰበውን መረጃ ሊያጣራና ሊያጠናክር ይገ<br>((ምንጭ፡- የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 1) |

| | | |
|---|---|---|
| | | 2.2.3 በማህበር ያልተደራጁ ሰራተኞች የስራ ላይ መብት አጠባበቅ አስመልክቶ በተዘጋጀ የመረጃ መሰብሰቢያ ፎርማት ሊቀርጽና ፣በናሙና ደረጃ ተግባራዊቱን ሊፈትሽና ስራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 1) |
| | | 2.2.4 የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በተመለከተ ከደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎች አይነትና ድግግሞሽ በመለየት መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 1) |
| | | 2.2.5 በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ግንዛቤ የሚያዳብሩ ፓስተሮች ፣ብሮሸሮች/በህትመትና በኤሌትሮኒክስ ዘዴ ሊያዘጋጅና ሊያሰራጭ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 1) |
| | | 2.2.6 በስራ አካባቢ የደረሱ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶች (ከፍተኛ /ከባድ ጉዳት ) ያስከተሉትን ስብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ለመገምገም እና ተመሳሳይ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ የሚያስችል የአደጋ ምርመራ / Accident investigation/ ሊያካሂድና የምርመራ ሪፓርት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 2 |
| 3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከተ የወጡ ህጎች፣ ደንቦች ፣ መመሪያዎችና እና አለም አቀፍ ስምምነቶች በስራ ላይ ስለመዋላቸውንና ውጤታማነታቸውን ለመገምገምና ለማስተካከል የሚያስችል የክትትልና ፣ የቁጥጥርና የግብረ መልስ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣ | | 3.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉ የስራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎችን ሊመድብ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 11) |
| | | 3.2 የስራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ በቴክኒክ ወይም በህግ ረገድ ጥርጣሬ የሚያሳድርበት ጉዳይ ሲያጋጥመው ወዲያውኑ አስፈላጊውን ውሳኔ እንዲሰጥበትና በውሳኔው መሰረት አስፈላጊውን ትዕዛዝ እንዲተላለፍ ለሚኒስተሩ ሊያቀርብ ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 14) |

| | | |
|---|---|---|
| | | 3.3 የስራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው ቁጥጥሩን ካካሄደ በኃላ በተቻለ ፍጥነት ደረጃውን የጠበቀ ሪፓርት አዘጋጅቶ ቁጥጥር ለተደረገለት ድርጅትና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ሊልክ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዲስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 31) |
| | | 3.4 የስራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች በማናቸውም ድርጅት አጥር ግቢ ውስጥ በፋብሪካ መሳሪያዎቹ ወይም እቃዎቹ ወይም የድርጅቱ ስራ በሚካሄድበት ዘዴ ምክንያት ለሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት አስጊ ሆኖ ሲገኝ ሁኔታውን ለማሻሻል አሰሪው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን እርምት ሊወስዱ ይገባል፣ (ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዲስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 13) |
| | | 3.5 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ሁኔታን የሙያ ደህንነትና ጤንነት እና የስራ አካባቢን በተመለከተ በአዋጅና በሌሎች ህጎች የወጡ ድንጋጌዎችን በተግባር መዋላቸውን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዲስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 31) |
| | | 3.6 የአሰሪና ሰራተኛ አስተዳደር የመረጃ አያያዝና አደረጃጀት ስርዓት እንዲዘረጋ ድጋፍና ክትትል ሊደረግ እንዲሁም አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዲስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 3) |
| | | 3.7 ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገር አቀፍ የስራ ቦታ እንቅስቃሴዎች በድርጅቶች የሙያ ደህንነትና ጤንነት የተከናወኑ ተግባራት እንዲሁም የኢንዲስትሪው ግንኑነት አገልግሎት መረጃዎች ሊሰበስብና ሊያደራጅ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዲስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 3) |
| | | 3.8 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በሚመለከቱ አዋጆች ፣ደንቦች እና መመሪያዎች ዙሪያ በግንባር እና በፁሁፍ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል (ምንጭ፡-የስላማዊ ኢንዲስትሪ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትየስራ ሁኔታ ቁጥጥር ማንዋል ገፅ 3) |
| | | 3.9 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አስተዳደር ሥርዓት በማቋቋም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን ለማዘጋጀት፣ ለማስተባበር፣ ለመከታተልና ለማስፈጸም የሥራ ሥምሪት አገልግሎት፣ የስራ ሁኔታዎች መቆጣጠሪያ አገልግሎት |

| | | |
|---|---|---|
| | | እና በመንግስት፣ በአሰሪዎች ማህበራትና በሰራተኞች ማህበራት መካከል ቋሚ የሆነ አማካሪ ቦርድ ሊያቋቁም ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ገፅ 190) |
| | | 3.10 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌደራልና በክልል የሚገኙ ድርጅቶችን ዝርዝር መረጃ ሊይዝ ይገባል፤<br>(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ገፅ 190) |
| | | 3.11 ሚኒስትር መ/ቤቱ የሙያ ዘርፉን ያገናዘበ የሙያ ደህንነትና የሙያ ደህንነትና ጤንነት መመዘኛ መስፍርት ( ስታንዳርድ) ሊከለስ ይገባል መሆኑ፣<br>(ምንጭ፡- (ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ገፅ 190) |
| | | 3.12 ሚ/ር መ/ቤቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መለኪያ እና መቆጣጠሪያ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡<br>(ምንጭ፡- (ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ገፅ 190) |

## <u>የሙያ ደህንነትና ጤንነት የስራ ክፍል ዝርዝር የስራ መግለጫ</u> አባሪ 2



# በናሙና የተመረጡ ክልሎችና የልማት ድርጅት ዝርዝር

## በናሙና የተመረጡ  ክልሎች

| ተ.ቁ | የክልሎች ዝርዝር | ከተማ/ወረዳ |
|---|---|---|
| 1. | ኦሮሚያ | የኦሮሚያ (የክልሉን ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ |
| 2 | አዲስ አበባ | አ/አበባ (ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ) |
| 3 | ደቡብ | የሀዋሳ (ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ) |

## በናሙና የተመረጡ ድርጅቶች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | በናሙና የተመረጡ  ድርጅቶች ዘርፍ | የድርጅቶች  ስም |
|---|---|---|
| 1. | ከኮንስትራክሽን ዘርፍ የግል ድርጅቶች | ✓ የኢትዮጲያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን<br>✓ የኢትዮጲያ መንገድ ኮንስትራክን<br>✓ ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>✓ ባማኮ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>✓ ዛምራኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር |
| 2. | ግብርና | ✓ ክሌቨር ፍላወር ኃ/የተ/የግል ማህበር |
| 3 | ማኒፋክቸሪንግ | ➢ ብሄራዊ ትንባሆ አክሲዮን ማህበር |
| 5 | ህትመት | ➢ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት |
| 6 | አገልግሎት | ➢ የኢትዮጲያ መብራት አገልግሎት<br>➢ የኢትዮጲያ የእህል ንግድ ድርጅቶች |
| 7 | ድርጅት | ➢ ታቦር ሴራሚክስ አክሲዮን ማህበር |
| 8 | ማህበራት | ➢ የኢትዮጲያ ሠራተኞች ማህበር ኮንፌዴሬሽን<br>➢ የኢትዮጲያ አሰሪዎች ፌዴሬሽን<br>➢ የኢትዮጲያ ኮንስትራክሽን ህንፃ ተቋራጭ ማህበር<br>➢ የኢትዮጲያ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራችና ላኪዎች ማህበር |